# ምዕራፍ ሃምሳ ዘጠኝ

## የጦርነቱ ኪሣራ ጥያቄ—በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል የተደረገው ውል

በሠለጠኑትና እኩያ በሆኑት አገሮች መካከል ጦርነት ሲደረግና አንዱ ወገን ሲሸነፍ፣ ተሸናፊው መንግሥት ብዙ ጊዜ በወሰን ያሉትን አከራካሪ መሬቶች ከማጣት በቀር ሁለቱ በተስማሙበት ግምት ተሸናፊው ለአሸናፊው የጦር ካሣ ይከፍላል። ይኸን ሁሉ የሥርዓቱንና የሕጉን አንቀጽ ጠቅሶ የሚከራከር ሒሳቡን በደንብ የሚተምን የተማረ የሰው ኃይል በኢትዮጵያ በኩል መጉደሉ የታወቀ ነው። በጦር ሜዳ ተሰልፎ በጀግንነት የሚዋጋው፣ እንደ ዘመኑ ልማድ አገር የሚያስተዳድረው፣ ዳኝነት የሚሰማው ተርፎ ተትረፍርፎ ሳለ፣ በዚህኛው ግንባር ግን፣ የአገሪቱ ደካማ ጐን ይታያል ማለት ይቻላል።

ስለዚህ፣ ዐፄ ምኒልክ ለዚህኛው ቴክኒክ ላለበት ጉዳይ ይጠቀሙ የነበሩት የአውሮፓን ሁኔታ የኢጣልያንም ሳይቀር እየተከታተለ የሚያስረዳቸው ብዙ ጊዜ ስሙን የጠቀስነው ሞንዶን ቪዳዬ ነው። ለጦር መማሪያ ግዥና አቀራረብ ሊዎን ሸፍነ፣ ወሰን ሳይኖርባቸው የቅርብ አማካሪዎች፣ እንግዳ አስገቢዎች በተለይ ዋናው የስዊሱ ተወላጅ አልፍሬድ ኢልግ ሲሆን፣ ከርሱም ጐን ሌዎንስ ላጋርድ፣ ሳቡሬ አርማንድ፣ ፒዬር አርኑ የሚባሉ ፈረንሳዮች ይገኙበታል። ከነዚህም ጐን ከዓድዋ ጦርነት በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ የተቀበለው ኒኮላ ሊዎንቴቭ የሚባለው የመስኮብ ተወላጅ አለበት።

እነዚህም የተለያዩ የውጭ አገር ዜጎች፣ አዲስ አበባ ሳሉ በንጉሠ ነገሥቱ ዙሪያ ሆነው የተለያዩ አገልግሎት ሲያበረክቱ በየአገራቸውም በሚቆዩበት ጊዜ፣ “ለምሳሌ ሊዎንቴቭ ፒዬትሮ ቡርግ (የዛሬው ሌኒንግራድ)፣ እነሸፍነና እነሞንዶን ፓሪስ፣ እነላጋርድ አቦክ (ጅቡቲ) በሚገኙበት ጊዜ ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ የሚነዙትን መጥፎ ወሬ በመቃወም፣ ለኢትዮጵያና ለንጉሠ ነገሥቱ የሚጠቅመውን አገልግሎት ያበረክቱ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱም ለያንዳንዱ የውጭ አገር አገልጋይ ከሚያደርጉት ሹመት፣ ስጦታና ሽልማት ጋር

ልባዊ ወዳጅነት ስለሚያሳዩት ፣ የውጭ አገሮች ዜጎች ኢትዮጵያን እንደ አገራቸው ፣ ምኒልክን እንደ ራሳቸው መሪ ይመለከቷቸው ነበር ። አልፍሬድ ኢልግ በሚጻጻፍበት ደብዳቤ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ባለሥልጣን የራሱ ማኅተም ነበረው ። በማኅተሙ መካከል የጽሑፍ ስሌዳ ሆኖ ከወደላይ ወገን በአማርኛ ፣ "ቢቶደድ ኢልግ" ሲል በታች በኩል "የመንግሥት አማካሪ" የሚል ይገኝበታል ። ከዓድዋ በኋላ ደግሞ ሙሴ ላጋርድ ቀድሞ የፈረንሳይ መንግሥት በጅቡቲ አገረ ገዥ የነበረው ከመንግሥቱ ተሰናብቶ ያፄ ምኒልክ አማካሪ በነበረበት ሰዓት ከመኳንንቱም ፣ ከማንም ጋር የሚጻጻፍበት ማኅተም ተመካከሉ ስሌዳ ያለው ሆኖ በስሌዳው ላይ አክሊልና ስሌዳውን ሁለት የቆሙ አንበሶች እንደሚደግፉት ሲታይ ፣ በላይ በኩል በግዕዝ "እግዚእ ዕቀባ ለኢትዮጵያ" የሚል ፣ በታች በኩል "ላጋርድ የእንጦጦ ዱክ" ይላል ። "እግዚእ ዕቀባ ለኢትዮጵያ" ማለት ጌታ (አምላክ) ኢትዮጵያን ጠብቃት" ማለት ነው ።

አሁን ከኢጣልያ ጋር የዕርቅ ድርድር በተጀመረበት ሰዓት አልፍሬድ ኢልግ ቀደም ብሎ ፣ ሊዎንቴቭ ከተል ብለው ሁለቱም ወደ ሮማ ሔደው የኢጣልያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ስለሚከፍለው የጦር ኪሣራ መነጋገር ጀምረዋል ።

ኢልግ ከአዲስ አበባ ወደ ዙሪክ (ስዊስ) ሔዶ ከዚያም ወደ ሮማ ዘልቆ ስለ ኪሣራውና ስለ እርቁ ጉዳይ በምኒልክ ስም ለመነጋገር በሚዘጋጅበት ጊዜ ፣ ባለቤቱ ማዳም ኢልግ ባሏ የምኒልክ ባለሟል አማካሪ በመሆኑ ፣ አሁን ሮማ ለመሔድ በሚያስብበት ጊዜ ፣ "በዓድዋ በኢጣልያኖች መሸነፍ የተበሳጩት ወገኖች ቢገድሉህስ" በማለት ተከላከላ ነበር ። ነገር ግን ፣ በወዳጁ በኢጣልያዊው በአወግስጦስ ፍራንዚይ አማካይነት ተጸጽፎ ማረጋገጫ ከተቀበለ በኋላ በሰኔ ወር ወደ ሮማ ሔደ ። ከዚያም ሊዎንቴቭ በነሐሴ (1888) ደርሶ ሁለቱም የኢጣልያ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ኪሣራ እንዲከፍል አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ማርኬዝ ዲ ሩዲኒን ቢጠይቁት ፤

> . . . የኢትዮጵያ መንግሥት ለምርኮኞች ያወጣውን ኪሣራ በመቶ ሺ ወይም በሚሊዮን የሚቆጠር ሊሬ ቢሆን እከፍላለሁ እንጂ የጦር ኪሣራ አልከፍልም ። በዚህ ምክንያት እስረኞቹ ቢቸገሩም ቢሞቱም እንደ ፈቀደው ። ምኒልክ የጦር ኪሣራ ከፈለጋቸው እዚሁ ሮማ ይምጡና በመጠየቅ ይሞክሩኝ . . .

ብሎ መቁረጡን ፣ ይኸንኑ ለንጉሥ ኡምቤርቶ ማመልከቱንና ንጉሡም አሳቡን እንደ ደገፈ ታወቀ ።



በአዲስ አበባም ፣ ይኸው የኢጣልያ መንግሥት አቋም በትክክል ከታወቀ ወዲህ ፣ ንጉሠ ነገሥቱና አማካሪዎቻቸው የራሳቸውን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ለማስፈጸም ያላቸውን አቋም በመገምገም ዋናው ፍሬ ነገር የዓድዋን ጦርነት ያስከተለውን የውጫሌውን ውል የኢጣልያ መንግሥት ሠርዞ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት ካወቀ ውሉ ይፈረም ፣ እስረኞቹም ተለቀው አገራቸው ይግቡ ተብሎ የውለታው ነገር እንዲፈጸም ተወሰነ ።

ውለታው በአማርኛና በፈረንሳይኛ ጐን ለጐን ሆኖ እንደሚከተለው ይነበባል ።

በኢትዮጵያ መንግሥትና በኢጣልያ መንግሥት ማኸል (መካከል) የተደረገ የዕርቅ ውል ይህ ነው ።

በቅድስት ሥላሴ ስም እንጀምራለን ።

ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክና በስም መጀመሪያ ኡምበርቶ የኢጣልያ ንጉሥ ጦርነት ለማስቀረት

ዱሮ የነበረውን ፍቅራቸውን መልሰ ለማደስ ስለወደዱ ከዚህ ቀጥሎ የሚጻፈውን ውል ተዋዋሉ ። ይህንንም ውል ለመዋዋል ከኢጣልያ ንጉሥ ሙሉ ሥልጣን የተቀበለ በሳንሞሪስዎ በሳንላዛር በኢጣልያም ዘውድ ኒሻን የተሸለመ ማጆር ዶክተር ሲዛር ኒራሴኒን መርጠው ላኩ ። የማጆር ኔራሲኒ ሥልጣን የተካከለ መልካም መሆኑ ስለታየ የከበረ ማጆር ኔራሲኒ በኢጣልያ ንጉሥ ስምና ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እርስዎ ተቀምጠው ቀጥሎ የሚጻፈውን ክፍል ሁሉ ተስማምተው ተዋዋሉ ።

## መጀመሪያ ክፍል

በኢትዮጵያና በኢጣልያ ማኸል የተደረገው ጦርነት ጭራሽ ቀርቷል ። እንዲህ ስለሆነ በኢጣልያ ንጉሥና በጃንሆይ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በወራሾቻቸውም ለዘላለም እርቅና ፍቅር ይኖራል ።

## ሁለተኛ ክፍል

በ25 ሚያዝያ በ1881 በውጫሌ ሰፈር የተደረገ ውልና በኋላ ታርሞ የተጨመረውም ውል ሁሉ ጨርሶ ተፍቋል ። እንደ ተፋቀም ጭራሽ ይቀራል ።

## ሦስተኛ ክፍል

የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን ነጻነት ራሱን የቻለ ባለ ነጻ መንግሥት መሆኑን ጨርሶ ተቀብሎአል ።

## አራተኛ ክፍል

እነዚህ ሁለቱ በዚህ ውል የሚዋዋሉ ነገሥታት ባገሩ ድምበር ነገር ሳይስማሙ ቢቀሩ በእርቁ ቶሎ ለመዋዋልና ለሁለቱም አገር የዕረፍት መልካም እርቅ ለማድረግ ስለወደዱ፤ እስከ ዓመት ድረስ ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና የኢጣልያ ንጉሥ የመረጡዋቸው ሽማግሎች በፍቅር ተስማምተው የወሰኑን ነገር እንዲጨርሱ ተዋውለዋል ። ወሰኑ እስኪወሰን ድረስ ግን፤ ሁለቱ ተዋደው ዛሬ ባሉበት በመቆያው ወሰን በመረብና በበለሳ በሙና ወንዞች ሳይተላለፉ እረግተው ይቆያሉ ።

## አምስተኛ ክፍል

የኢትዮጵያና የኢጣልያ መንግሥት ተስማምተው እስኪጨርሱ ድረስ የኢጣልያ መንግሥት ከዚህ አገር ለማንም ግን መንግሥት መስጠትና መልቀቅ አይቻለውም ። ዛሬም የኢጣልያ መንግሥት በጁ ከያዘው አገር መልቀቅ ያማረውም እንደሆነ ለኢትዮጵያ መንግሥት ይመልሳል ።

## ስድስተኛ ክፍል

የኢትዮጵያ መንግሥትና የኢጣልያ መንግሥት የጥበብና የንግድ ሥራ ለመርዳት ቢፈልጉ ሁለቱ መንግሥታት ተስማምተው ውሉን ኋላ ማድረግ ይመቻቸዋል ።

## ሰባተኛ ክፍል

ይህ አሁን የተደረገው ውል እነዚህ ሁለቱ የተዋዋሉ ነገሥታት በጥንቃቄ ለሌሎቹ ነገሥታት ያስታውቃሉ ።

## ስምንተኛ ክፍል

ይህም አሁን ያደረግነው ውል ከዛሬ አንሥቶ ለ3 ወር ድረስ በኢጣልያ መንግሥት ፈጽሞ ይታተማል ።

## ዘጠነኛ ክፍል

ይህ ዛሬ የተደረገው የዕርቅ ውል ተካክሎ ባማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ ከሁለት ላይ ይጻፋል ። ታትሞም ሲያበቃ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና በኢጣልያ ቤተ መንግሥት ይቀመጣል ።

በዚህ ተስማምተው ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እርስዎ ራስዎና የከበረ ማጆር ኔራሲኒ በኢጣሊያ ንጉሥ ስም ተቀብለው በየማኅተማቸው ይህን ውል አተሙ ።

በጥቅምት በ17 ቀን ተጻፈ ባዲስ አበባ ከተማ በ1889 ዓመተ ምሕረት ።



# ምዕራፍ ስድሳ

### የምርኮኞቹ አኗኗር — ስለነርሱ የተደረገው ስምምነት ስለወጣው የኪሣራ ገንዘብና የምርኮኞቹ አገራቸው መግባት

ስለ ምርኮኞቹ በተለይ የተደረገውን ውል ከማንበባችን በፊት፤ ወደ ኋላ መለስ ብለን ከዓድዋ እስከ አዲስ አበባ ባደረጉት ጉዞ ከነጻነታቸው በፊት በኢትዮጵያ ተበታትነው በየመኳንንቱ ቤት በምሪት በነበሩበት ሰዓት የሆነውን መመልከት ታሪኩን የበለጠ የሚያሟላው ይመስላል ።

በዓድዋ ጦርነት ወደ መገባደጃው ላይ የመድፍ፤ የመትረየስና የጠመንጃ ድምፅ ጋብ ሲል እግረኛም፤ ፈረሰኛም ጣልያኖችን እያራወጠ ሲከብ፤ ሲያባርርና ሲማርክ የሆነውን አስደናቂ ትርዒት ለዛሬ ታሪክ አንባቢ እንደ ብርቅ ስሌዳ ሆኖ በመገረም ዐይንና ሕሊና ሊታይ ይችል የነበረውን አስገራሚ ሁኔታ የኛዎቹ አሸናፊዎች በዝርዝር በጽሑፍ ሊያወርሱን አልቻሉም ። በልዩ ልዩ ሞያና በሥነ ጽሑፍ፤ በአስተዳደር ዘዴ የሠለጠኑት፤ በልማት የበለጠጉት፤ በዚህ ቀን ሳያስቡትና ሳይጠብቁት የመሸነፍ አደጋ የደረሰባቸው ወገኖች ግን ሁኔታውን በማስታወሻ መዝግበውት ይገኛል ።

ከነዚህም ውስጥ ማዦር ጂዮቫኒ ጋሜራ፤ ቴኔንቲ ዠራልዶ ፖንታኖ (በኋላ ዤኔራል)፤ ሐኪም ኒኮላ ዳማቶ፤ ሴርጀንቲ ጂዮቫኒ ቲዶኔ፤ ፍራንቼስኮ ፍሪዚና ሉዊጂ ጉይ ስድስቱ ከምርኮኞቹ ውስጥ የነበሩት የተዉት ማስታወሻ በመጨረሻ ጊዜ ለተነሡት ታሪክ ጸሐፊዎች ለነሉካ ዴይሳቤሊ፤ ለነኮንቲ ሮሲኒ ለነአንጀሎ ዴልቦካ ጠቅሟል ። ማዦር ጋሜራን የማረከው አንድ የባሻነት ማዕረግ ያለው የራስ መኰንን ጭፍራ እንደ ነበረና ከማረከው ዠምሮ ባሻው በጎ ነገር እንዳደረገለት፤ ከዚያም የራስ መኰንን ልጅ ይልማ (በኋላ ደጃዝማች) የሱፍ ብርድ ልብስ ሲሰጡት፤ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደ ኮረጆ ያለ ዕቃ መያዣ እንደ መጸወቱት፤ አፈ ንጉሥ ነሲቡ እጅ የወደቀው የመቶ አለቃ ፖንታኖ የበለጠ ዕድለኛ በመሆን ከተማረከበት ሰዓት አንሥቶ አፈ ንጉሡ እንደ ልጃቸው እንዳንከባከቡት፤ "ሁለት ጠላቶች እያንዳንዳቸው ግዳጃቸውን ከፈጸሙ በኋላ ሊወዳጁ መቻላቸውን" ጠቅሰው፤ "እንግዲህ ይኸኛውን ልጄን (ደጃች ደምስ በኋላ ራስ)

ባለቤቴ ሰጥታኛለች ። የአንተን ልጅነት ደግሞ እምላክ ሰጥቶኛልና የሚያስፈልግህን ጠይቀኝ” ብለውት ፣ በዚያ አስቸጋሪ በሆነው ከዓድዋ እስከ አዲስ አበባ በተደረገው ጉዞ ላይ የሚተኛበት የበሬ ቁርበት ፣ እንደ ጋቢ እጀ ጠባብና ኩታ እንደሰጡት ፤ ለጄኔራል አልቤርቶኒ የሚጓዝበት ፈረስ ፣ የሚያድርበት የተለየ ድንኳንና አገልጋዮችም ተሰጥቶት እንደነበር ፤ ሁሉም ለተሰጠው ምርኮኛ መንከባከብ እንዲያደርግ ከንጉሠ ነገሥቱ መመሪያ ትእዛዝ ተሰጥቶ እንደ ነበረ ያወሳል ።[1]

እነዚሁ ምርኮኞች በተዉት ማስታወሻ ላይ ፣ ጉዞው ሁለት ወር (ሚያዝያና ግንቦት) እንደፈጀ ፣ በመንገድ ላበሾቹም ለምርኮኞቹም ስንቅ አልቆ በየመንገዱ ሰው ይሞት እንደነበረ ፣ ከኢጣልያኖቹም ውስጥ ከዐርባ እስከ ሠላሳ የሚሆኑ ቁስለኞች በመንገድ ሞተው እንደ ተቀበሩ ፣ የጉዞውና የረኃቡ ችግር ሁሉንም ስለ ጠመደው ፣ አሽናፊዎቹ ለራሳቸው አድልተው በምንም ዓይነት ምርኮኛውን እንዳልበደሉ ፣ ሁሉም በጉዞው ላይ በመልካም ዐይን እየተያየ አልፎ አልፎ እውሬ እየታደነ ይበላ እንደነበረ ፣ አንዳንድ ምስኪን ባላገሮችም “ውሀ ፣ ዕንቁላልና ዶሮ ለነዚህ ፈረንጆች እንስጣቸው” እያሉ ይሽቀዳደሙ እንደነበሩ ፤ ከሁሉ የበለጠ ደግሞ በጉዞ ላይ እንጀራና ዳቦ እንዲታደላቸው በማድረጋቸው የእቴጌ ጣይቱን ቸርነት በማስታወስ የጉዞውን ሁኔታ ፍሪዚና ፍራንቼስኮ የሚባለው ተጓዥ ምርኮኛ ባይኑ ያየውን እንደዚሁ ሲል ገልጾታል ።

> ...የግንባር ቀደሙ ጦር በፊታውራሪዎቹ ይመራል ። ከግንባር ቀደሙ ጦር ኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በብር ዕቃ ባጌጠች ጥሩ በቅሎ ላይ ተቀምጠው በታላላቅ አለቆች ፣ በፈረሰኞችና በግል ዘበኞቻቸው ታጅበው ይጓዛሉ ። እንደ ዘወትሩ የሐር ካባ ደርበው የራስ ማሰሪያ (ሻሽ) አስረው ፣ በዚያ ላይ ስፊና ዝርግ ጥቁር ባርኔጣ አድርገው የፀሐዩ ሙራ እንዳያስቸግራቸው በፈረስ ያሉ ሰፋፊ ጃንጥላ ይዘው ይከልሏቸዋል ። ከርሳቸው ኋላ ጣይቱ ሁለመናቸውንና ፊታቸውን በሐር ጨርቅ ተሸፍነው ሲጓዙ ....

ከርሳቸው ኋላ ደግሞ ብዙ ራሶች በየግል ጭፍሮቻቸው ታጅበው እንደሚጓዙ ፣ ከነርሱም ጋር ካህናትና የበታች ሹማምንት ግማሽ በፈረስ በበቅሎ በግመልም የሆነው የበረከተ መሆኑን ፣ የጭነት አጋሠሥና የአህያውን ብዛት በጠቀሰበት ላይ ሁለት የጭነት ዝ
ኖች እንደ ነበሩና እንደዚህ ሆኖ ይጓዝ የነበረው ሁሉም ቅልጥፍ
እንደነበረው ያወሳል ።

1 Venti Anni di Vita Africana, Gen. Pantano, PP. 74 - 81; Gli Italiani in Africa PP. 719 -722.



በዚህ ዐይነት ምርኮኞቹ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ፣ በየመኳንንቱ ቤት ተመርተው አብዛኞቹ በነዚያው ከዓድዋ ዝምሮ ባመጧቸው መኳንንት እጅ እንዲቆዩ ሲደረግ ፣ ዋናው ጄኔራል አልቤርቶኒ በአዛዥ ዛማኄል (ዘአማኑኤል) እጅ ተመርቶ ደንበኛ የምርኮኝነት እንክብካቤ አልጎደለበትም ። የቀሩትም ከንጉሠ ነገሥቱ በተሰጠው መመሪያ መሠረት በተቻለ መጠን የበሬና የበግ ሥጋም ዶሮና እንቁላል እንደዳረጐት እየተሰጣቸው ፣ ግማሾቹም ራሳቸው እየሠሩ ሲቀለቡ ከርመዋል ። በዚህ መካከልም አንዳንዶቹ ቅሚያና ሴት ጉተታ እያበዙ ፣ ከጠባቂዎቻቸው ጋር ጠብ እያበቀሉ ያስቸገሩም አሉ ።

ከላይ የተጠቀሰው ፍሪዜና ፍራንቼስኮ የሚባለው የሃምሳ አለቃ ጠባቂውን ደብድቦ በዚሁ ተይዞ ራስ ዳርጌ ላይ በቀረበበት ሰዓት ፣

> ...እግዚአብሔር ዓድዋ ላይ ቀጣችሁ ። አሁን እስረኞች ሆናችሁ ሳለ እናንተ አረመኔ እያላችሁ ትሰድቧቸው የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ራርተው በመልካም ብትያዙ እናንተ አበዛችሁት ።... ጠባቂዎቻችሁን እየተሳደባችሁ ትማቱ ዝመር...?

ሲሉ ያቀረቡለትን ተግሣጽ ጓደኛው ሉዊጂ ጉይ የተወውን ማስታወሻ ዴልቦካ አብራርቶ ጽፎታል ።[1]

እንደዚህ ሆነው ከቆዩ በኋላ ፣ ለምርኮኞቹ ከኢጣልያ አገር እነርሱን ለመርዳት በተቋቋመው ኮሚቴ አማካይነት በማገርር ኔራሲኒ እጅ ጥሬ የማሪያ ቴሬዛ ብርና ልዩ ልዩ ልብስ ከታደላቸው ወዲህ ፣ ልብሳቸውንና ጫማቸውን በመለዋወጥ እያማረባቸው ሔደ ። በመጨረሻም ስለ ሁለቱ መንግሥታት የወደፊት ወዳጅነትና ግንኙነት በጥቅምት 17 ቀን 1889 ዓ.ም. ደንበኛ ውል እንደ ተደረገ በዚሁ ቀን ምርኮኞቹን በሚመለከተው ጉዳይ ከዚህ እንደሚከተለው ተዋዋሉ ። የውሉ አርእስቱና መቅድሙ እንደ ፊተኛው ሲዝምር አንቀጾቹ በትክከል እንደዚህ የሚሉ ናቸው ።

## መዠመሪያ ክፍል

በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥት ማኸል ዛሬ ስለ ተደረገው የዕርቅ ውል በኢትዮጵያ መንግሥት እጅ ያሉ የኢጣልያ ወታደሮች ምርኮኞች ተሰቀዋል ። ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እነሂን ምርኮኞች በማፍጠን (በፍጥነት) ሰብስበው ሲያበቁ ይህ የዕርቅ ውል ተጠንቅቆ* ታትሞ ሲመጣላቸው ሐረርጌ ላይ ከኢጣልያ መንግሥት ሙሉ ሥልጣን ተቀብሎ ለመጣው ሰው ያስረክባሉ n

1 Gli Italiani in Africa ... PP. 726 - 728.

* ጸድቆ ከኢጣልያ አገር ሲመለስ

## ሁለተኛ ክፍል

እነዚህ የጦር ምርኮኞች ወዳገራቸው ሲመለሱ እንዳይቸገሩ ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኢጣልያ የቀይ መስቀል ማኅበር ጂልዴሳ* ድረስ መጥተው እንዲቀበሏቸው ይፈቅዱላቸዋል ።

## ሦስተኛ ክፍል

የኢጣልያ ንጉሥ መልክተኛ እኒህ ምርኮኞች ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በብርቱ አቀማመጥ ማስቀመጣቸውን እሱ ራሱ ስላየ እንዲሁም እድርጎ አቀማመጡ ለማስቀመጥ ብዙ ገንዘብ እንደ ፈጁ ስለዐወቀ ፡ ይኸነን ስለኒህ ያወጡትን ገንዘብ የኢጣልያ መንግሥት እንዲከፍል ባለዳ መሆኑን ተቀብሏል ። ጃንሆይ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግን ፡ የገንዘቡን ኪሣራ ነገር የኢጣልያ መንግሥት እንዳ ወቀ ፈርዶ ሊሰጣቸው (እንዲሰጣቸው) ፍርዱን በኢጣልያ መንግሥት ላይ ጥለውታል ።

በዚህ ውል ተስማምተው ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እርስዎ ራስዎና የከበረ ማዦር ኔራሲኒ በኢጣልያ ንጉሥ ስም ተቀባብለው በየማኅተማቸው ይህን ውል አተሙ ። በጥቅምት 17 ቀን 1889 ዓ. ም. ተጻፈ ።

ከዚህ ውል ዝምሮ እስረኞቹ ሙሉ ነጻነት አግኝተው ከአዲ አበባ ውጭም ፡ በአዲስ አበባም ያሉት አዲስ አበባ ላይ ተሰብ በው ወደ ሐረር የጉዞው ነገር በትጋት ተያዘ ። ስለ ኪሣራው አቀ በልም በሁለቱ መንግሥታት ወኪሎች መካከል ንግግር ሲደረግበ በሰነበተበት ሰዓት ፡ ከኢትዮጵያውያኑ ወገን ከሠላሳ እስከ ዐርባ ሚ ዮን ሊሬ ሲጠየቅ ፡ ምኒልክ ዐሥራ ሁለት ሚሊዮን እንዲሆን ማ ባቸውን ፡ "ይኸማ ከዚያው ከጦር ካሳ የበለጠ ሆነ" የሚል ከ ራሲኒ በኩል ከርክር ቀርቦ በአራት ሚሊዮን ላይ እንዲመደብ ተ ራከረ ። በመጨረሻ ሁለቱም ወገኖች ዐሥር ሚዮን ሊሬ እንዲሆ ተስማምተው ይኸም ያለወለድ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እ ዲከፈል ተስማሙ ።[1] በዚያን ዘመን ምንዛሪ አንዱ የማሪያ ቴሬ ብር አራት ሊሬ ስለሆነ ፡ ከፍያው በማሪያ ቴሬዛ ብር ሲታሰብ ወ ሁለት ሚሊዮን ተኩል ይሆናል ማለት ነው ።

በተረፈ ማዦር ኔራሲኒ ከዚህ በላይ የተደረገውን የሰላምና የ ዳጅነት ውል ከደረገ ወዲህ ፡ እላይ እንዳልነው እስረኞቹ ተከፋፍለ

---

* ጊልዴሳ ወይም ጀልዴሳ በድሬዳዋና በዘይላ መካከል የሚገኝ ፈሳሽ ወንዝ የሚ ኝበት ትንሽ ከተማ ነው ።

I Gli Italiani in Africa Orientale, PP. 731 - 732 ; Storia Diplomatica . . . . . . C. Rossetti, Chap. VII. PP. 181—206



ከየተላኩበት እንዲሰበሰቡና ሐረር ላይ እንዲጠራቀሙ ተደረገ ። ከነ ዚሁ ውስጥ አራት የሚሆኑት የኢጣልያ ምርኮኞች ከጄኔራል አል ቤርቶኒ ጋር አዲስ አበባ ነበሩ ።

ማዦር ኔራሲኒ ከዘይላ ወደ ሐረር ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በመጣበት ጊዜ ፡ ከኢጣልያ አገር ለምርኮኞቹ አስፈላጊያቸውን ነገር መግዣ ከኢጣልያ መንግሥት ዘንድ ዐርባ ሺ የማሪያ ቴሬዛ ብር እንደዚሁም የሮማ እመቤቶች እያዋጡ የላኩት ልዩ ልዩ ጥቅል ዕቃ መጥቶ በየጊዜው ለምርኮኞቹ ታደለ ። ከዚያ የውሉ ቃል በኢጣልያ መንግሥት ከጸና በኋላ ፡ ቁጥራቸው አንድ ሺ ስድስት መቶ የሚሆኑት የኢጣልያ ምርኮኞች ከኢጣልያ አገርና ከምጥዋ ሊቀበሏቸው በመጡት በቀይ መስቀል ሠራተኞችና በሌሎችም ትጋት በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖችም አጋዥነት ከአዲስ አበባ ሐረር ፡ ከዚያም በጀልዴሳ በኩል አድርገው ወደ ዘይላ ፡ ከዘይላ ወደ ኢጣልያ አገር በሰላም ተጓዙ ።

ከአዲስ አበባ በተነሡ ጊዜ ፡ ለኢጣልያኖቹ በሙሉ ንጉሠ ነገሥቱ ባሉበት የመሰናበቻ ታላቅ ግብር ተደርጎ ግብሩ እንዳለቀ በምርኮኞቹ ስም ጄኔራል አልቤርቶኒ የምስጋና ዲስኩር አድርጎ ሲጨርስ ኢጣልያኖቹ ተነሥተው ፡ "ምኒልክ ሕያው ይሁን!" ብለው ደጋግመው እየጮሁ አመሰገኑ ።

የዓድዋ ዕለት በቀኝ በኩል አዝማች ሆኖ ሲዋጋ የሞተው የጄኔራል አሪሞንዲ ሻምላ ተማርኮ የነበረውንም "ለዘመዶቹ ለመታሰቢያ እንዲሆናቸው ስጥለት" ብለው ንጉሠ ነገሥቱ ለጄኔራል አልቤርቶኒ አስረከቡት ። ጠላቶች የነበሩት የኢጣልያን ምርኮኞች በዚህ ዓይነት ደስታ ፡ እርቅና ሰላም ወዳገራቸው ተመለሱ ።

በዓድዋ ጦርነት የተማረኩትን ቁጥራቸውን የሚያበዛውና የሚቀንሰው አለ ። ያበዛው እስከ ሁለት ሺ ፡ ያሳነሰው እስከ አንድ ሺ አምስት መቶ ያደርሰዋል ። ነገር ግን ፡ በጣም የቆሰሉና የማይሔዱ ምርኮኞች በትግሬ በየመንደሩ ተመርተው ይታመሙ ከነበሩት ውስጥ ግማሾቹ የሞቱ ፡ ግማሾቹ በራስ መንገሻ ትእዛዝ ለጄኔራል ባልዲሠራ ተሰጥተው ወደ አሥመራ ተልከዋል ። አንዳንዶቹ በንጉሠ ነገሥቱ ጦር እየተጠበቁ ወደ አዲስ አበባ ሲጓዙ በመንገድ የሞቱ እንዳሉ በሰፊው ተመልክቷል ። አዲስ አበባም ከደረሱ በኋላ በየአውራጃው ለየሹማምንቱ ተመርተው የሰላሙ ውል እስኪፈጸም ድረስ አንዳንድ ሕይወታቸው ያለፈ ይገኝባቸዋል ። ከዚህም በተጨማሪ ባለፈው የሐምሌ ወር በምምንቱ

ከመፈረሙ በፊት የመስኮብ ንጉሥ ኒኮላ የነገሡበትን ዕለት ባከበሩበት ጊዜ ስለርሳቸው ክብር ሃምሳ ምርኮኞች ተለቀው በጅቡቲ በኩል ወደ አገራቸው እንዲገቡ ተደርገዋል ።[1]

ስለዚህ ፣ ኤሚሊዮ ቤላቪታ የሚለው ትክክል እንደሆነ የሰላሙ ውል ከተፈረመ በኋላ ወደ አገራቸው የተመለሱት አንድ ሺ አንድ መቶ ዐርባ አምስት ፤ ከነዚሁ ውስጥ ሃምሳ ከፍተኛ የጦር መኰንኖች ፣ ሃምሳ አንድ ዝቅተኛ መኰንኖች የሚገኙበት ከአዲስ አበባ የተለቀቁ ሲሆኑ ፤ መቶ ሃምሳ ሐረር በራስ መኰንን እጅ የነበሩ ተጨምረው ነው ።[2]

እነዚህ ሁሉ ከኢጣልያ አገር በመጣው የቀይ መስቀል ድርጅት እየተረዱ ከዘይላ ወደብ ተሳፍረው በሚያዝያና በግንቦት ወር 1889 ዓ.ም. ላይ አገራቸው ገቡ ። አንዳንዶቹ ሹማምንት ወዳገራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ከጠባቂዎቻቸው የኢትዮጵያ መኳንንት ጋር በፍቅር ፣ በደስታ ተሰነባብተው ሲሔዱም ከየጠባቂዎቻቸው ለቤተሰቦቻቸው ደብዳቤ ይዘው የሔዱ ይገኙባቸዋል ። ከዚህ በፊት ስሙን ያነሣነው ፓንታኖ የሚባለው የመቶ አለቃ ምርኮኛ ዓድዋ ላይ በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ ለአፈ ንጉሥ ነሲቡ ተሰጥቶ ይዘውት ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሳለ ፣ ወዳገሩ ሲመለስ ለእናቱ እንዲያደርስ የሰጡት ደብዳቤ እንደዚህ ይላል ።

> . . . ልጅሽ ተማርኮ በእኔ እጅ ቆይቶ ነበር. . . በዚያ በተማረከበት ቀን ንጉሠ ነገሥቱ ለኔ አደራ ብለው ሰጡኝ ። እኔም ጃኖ ኩታ አልብሸ በፈረስ አስቀምጬ ወዳገሬ (አዲስ አበባ) አመጣሁት ። እኔም አንድ ቀንም ሳላስርበው ዓመቱን ጠጅ እያጠጣሁ ትኩስ ሥጋ እያበላሁ አኖርሁት ። አሁን ግን ፣ የእግዚአብሔር ምሕረት ወርዶ ባንቺም የፍቅር ጸሎት ይኸው ልጅሽን ልኬልሻለሁ ። መድረስ አለመድረሱን እግዚአብሔር ያውቃል ። ወዳንቺ በደህና መድረሱን አረጋግጭልኝ ። ይኸን ሁሉ ለልጅሽ ማድረጌ እኔም ልጆች ስለ አሉኝ ነው ።

ባለቤታቸው ወይዘሮ ደስታም በበኩላቸው ፤ "ባንቺ ውቃቢ በእግዚአብሔር ምሕረት ልጅሽ ከሞት ተርፎ መጥቶ በዐይኑ ሥጋ ልትገናኙ ነው ። መድረሱንና ካንቺ መገናኘቱን ጻፊልኝ ።" የሚል ጽፈዋል "[3] ። በዚህ ዐይነት ምርኮኞቹ በተለይ ሹማምንቱ በመልካም ተይዘው እንደነበር ለመረዳት አያዳግትም ።

1 Storia Diplomatica . . .P. 19
2 Adua . . , PP. 445 - 446.
3 Meoelik II, L' Etiopia eled Relazioni Con Italia, Falcooe, P. 132





አፈ ንጉሥ ነሲቡ
ከሞሪስ ደኮፒ መጽሐፍ

# ምዕራፍ ስድሳ አንድ

## ከዓድዋ በኋላ የኢትዮጵያ ነጻ መንግሥትነት በይፋ መደላደል — የኃያላን መንግሥታት እንደራሴዎች ወደ አዲስ አበባ መምጣት—ያቀባበሉ ሥነ ሥርዓት

ከብዙ ጊዜ ክርክርና ከብዙ ደም መፋሰስ በኋላ ጥቅምት 17 ቀን 1889 ዓ.ም በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገው የሰላም ውል በውስጡ የተዘረዘሩት አንቀጾች ግልጽ ስለሆኑ ፣ ስለነርሱ ሰፊ ሐተታ ማድረግ አያሻም ። ባንደኛው አንቀጽ የጄኔራል ባራቲዬሪ ጦር በዓድዋ ከተሸነፈ በኋላ ፣ ጄኔራል ባልዲሠራ በርካታ ጦር ይዞ ስለመጣ እንደገና ይዋጋና ሌላ ደም መፋሰስ ይቀጥል ይሆናል ተብሎ ይጠረጠር የነበረው ተወግዶ ሰላም መተካቱ ተገልጿል ። በሁለተኛው አንቀጽ ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም በተደረገው የውጫሌ ውል መሠረት ኢጣልያ ፣ "በኢትዮጵያ ላይ የበላይነትና የጠባቂነት መብት አለኝ" ብላ አጥብቃ የተከራከረችበት ውል በፍጹም መሰረዙ ፣ በሦስተኛው አንቀጽ የኢትዮጵያን ፍጹም ነጻ መንግሥት መሆኗን ማውጇ ተመልክቷል ።

ስለዚህ ከዐፄ ዮሐንስ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ላይ አንዣበ የነበረው የኢጣልያ የገዥነት ምኞት ለጊዜው ተዘጋ ። ለኢትዮጵያም አንድ የድል አድራጊነትና በራስ የመተማመን መንፈስን የያዘ ከፍ ያለ ታሪካዊ የክብር ገጽ በዓለም ታሪክ ፊት ተከፈተ ። ከ16ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ በተለይ ይህ 19ኛው መቶ ዓመት ለአውሮፓውያን መንግሥታት የወራሪነት ፣ ለደቡብ አሜሪካ ፣ ለእስያና ለአፍሪካ አህጉር የተወራሪነት ዘመን ነበረ ። በተለይ በአፍሪካ ሁሉም ሲወረር ፣ ከመወረር የተረፈች አገር ኢትዮጵያ ስትሆን ቅኝ አገር ያልደረሳት አገር ኢጣልያ በመሆኗ ፣ የነዚህ የሁለቱ አገሮች ክርክርና ጦርነት በዚህ ዓይነት ሲፈጸም አብዛኛው የዚህ የውል ጥቅም ለኢትዮጵያ ያመዝናል ማለት ይቻላል ። ይኸም ጥቅም የተገኘው ከዓድዋ ድል ሲሆን ድሉም የተገኘው በዚሁ ጦርነት ሕይወታቸውን በደስታ

በሠዉት አባቶች ነው ። ይህ ድል አድራጊነት የንጉሠ ነገሥቱ ፣
የእቴጌይቱ ፣ የመሳፍንቱ ፣ የመኳንንቱና የሹማምንቱ ብቻ ሳይሆን
ማር ገባሩም ፣ እህል ጫኙም ፣ ገረዱም ፣ አሽከሩም ፣ በቅሎ ለንጉ
ውም ፣ እንጨት ፈላጩም ፣ ውሀ ቀጅውም ሣር አጫጁም ሁሉም
ለዚህ ድል ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጓል ። ለዚህ ጦርነት ሕይወቱን
የሠዋው የሸዋ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ትግሬው ፣ ጐጃሜው ፣ ቤጌምድ
ሬውና ስሜነኛው ፣ ወሎዬው ወለጋው ፣ አሩሲው ፣ ሐረርጌው ፣ ጋሞው፣
ሲዳሞው ፣ ከፋው ፣ ከምባታው ፣ ወላይታው ሐድያው ስለ ተካፈለ ፣
የዚህ ድል አድራጊነት ክብሩም ኩራቱም የጋራ የኢትዮጵያውያን
ሁሉ ነው ።

በዚያን ጊዜ በነበረው የዓለም ሁኔታ በአውሮፓ ፊት አፍሪካ
ለተገዥነት የወደቀ ሲሆን ፣ በነጭ ዘንድም ጥቁር የተናቀና ነጭን ለማ
ገልገል በባሕርዩ የተመደበ ፣ ራሱን የማይችል ፣ ነጻነት የማይገ
ባው ሆኖ ይታመን ነበር ። የዚህን እምነት እንኳን ጠላቶቻች
ንና ከጠላቶቻችን ወገን የሆኑት እንግሊዞች ቀርተው ለኢትዮጵያ ያግ
ዛሉ የሚባሉት ፈረንሳዮች እንኳን ይነስ ይብዛ ያምናሉ ። ስለዚህ
የአፍሪካ አህጉር ባለቤት እንደሌላት ፈረንሳይ ፣ እንግሊዝ ፣ ጀርመን፣
ኢጣልያ ፣ እስፓኝ ፣ ፖርቱጋል ፣ ቢልዥክና ሌሎች ሰባት አገሮች እ.ኤ.አ
በ1884—1885 ዓ . ም በበርሊን ስብሰባ አድርገው አፍሪካን ለመከ
ፋፈል የሚያስችላቸውን የያዙትን አገር የሚያጠብቁበት ውሳኔ
እንዳሳለፉ የሚታወስ ነው ።

በ19ነኛው መቶ ዓመት ፣ ዓለም በዚሁ የገዥነትና የተገዥ
ነት መካከል እያለ በአፍሪካ ኢትዮጵያውያን የአውሮፓን ኢጣል
ኞች በጦርነት አሸንፈው መለሱዋቸው ። ግማሾቹን ማርከው በውል
ለቀቁዋቸው ። ያገራቸውን ነጻ መንግሥትነት አደላድለው ያዙ ሲባል ፣
በገዥው በአውሮፓና በሚገዛው በእስያና በአፍሪካ ሕዝብ ዘንድ የድሉ
ዜና እንደ ብርቅና ድንቅ ሆኖ ነው የተገመተው ። ከዚህ በፊት እን
ዳልነው ፣ ቅኝ አገር ያላቸው መንግሥታት የሌላቸውም ቢሆኑ የነጭን
ውርደትና ጥቃት ከልብ ባለመቀበል የዓድዋ የድል ወሬ ለአብዛኞቹ
መራራ ወሬ ሳይሆን አልቀረም ። መራራም ባይሆን ቅርታን መፍጠሩ
የማይጠረጠር ነው ። ከነጮች ውስጥ ባለፈው ጊዜ ደጋግመን እንዳመ
ለከትነው ፣ መስኮብ በሃይማኖት አንድነት ፣ ፈረንሳይም ከእንግሊዝና
ከኢጣልያ ጋር ባላት የፖለቲካና የጥቅም ግጭት የተነሣ ፣ ለኢትዮጵያ
ማገዛቸውን እናስታውሳለን ። ይሁን እንጂ ፣ የዓድዋ ድል የተከና



ወነው በመሠረቱ በወዳጅ አገሮች እርዳታ ሳይሆን ፣ የአሚሚታቸውን
ዓይነት ባየነው በነዚያ ባባቶቻችን ደምና መሥዋዕትነት ነው ። በዚያ
ቅኝ አገዛዝ በሰፈነበት ዘመን አባቶቻችን የማይናቁና ነጮችን ለማገ
ልገል በፍጹም ያልተፈጠሩ መሆናቸውን ከጥንት ታሪክ ተያይዞ
በመጣው መሠረት ነጻነትና እኩልነት የሚገባቸው መሆኑን በጽሕፈ
ትና በንግግር ሳይሆን በደማቸው አስመሰከሩ ።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከጃፓን ፣ ከቻይና ፣ ከታይላንድ በቀር
የቀረው የእስያና የአፍሪካ ግዛት ነጻነቱን ተገፎ በእንግሊዞችና በፈ
ረንሳዮች ፣ በቱርኮችና በሌሎችም ተከፋፍሎ ሲገዛ ኢትዮጵያ ነጻ
አገር ነበረች ። በኢትዮጵያ ላይ ቀደም ብሎ ከመሳፍንት ዘመን
ወዲህ ምንም እንኳን እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ቆንሲል አልፎ
አልፎ መላካቸው ባይቀር ፣ አንድ ጊዜ ቱርኮች ወይም ግብጾች
አለዚያም እንግሊዝ ከዛሬ ነገ ግዛታቸው ያደርጉታል እየተባለ
ማመንታት ስለነበረ ፣ አንድም መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ደንበኛ
የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ለማድረግና ነዋሪ ሚኒስትር ወይም አም
ባሳደር ልኮ ለማስቀመጥ ያቀደ አልነበረም ።

ግብጾችን ዐፄ ዮሐንስ ድል አድርገው ከመለሷቸው ወዲህ ፣ ኢጣ
ልያኖች በቱርኮችና በግብጾች እግር ተተክተው ከፍ ባለ ድርጅት
ኢትዮጵያን በሙሉ ለመያዝ ከግብጾች የበለጠ ምኞትና ተግባር አሳይ
ተዋል ። የነርሱንም በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት እቅድ ሁኔታ ኋያ
ላኑ የእንግሊዝና የጀርመን መንግሥታት መደገፋቸው ይታወቃል ።
ሌሎች መንግሥታት በዝምታ በሩቁ ሁኔታውን ከመመልከት በቀር
ደንበኛ የዲፕሎማቲክና የወዳጅነት ግንኙነት ለማድረግ እምብ
ዛም የጣረ መንግሥት አልነበረም ።

በዚህም ላይ ኢትዮጵያ ከአክሱም ዘመን ጀምሮ ቀዋሚ ታሪክ
ያላት አገር መሆኗን አውሮፓውያን ቢያውቁም ፣ ባሁኑ በ19ነኛው
ዘመን ተደራጅቶ በኃይል የተነሣባትን የሠለጠነ አውሮፓዊ መን
ግሥት በሥልጣኔ ኋላ ቀርነት የታወቀችው ኢትዮጵያ በኃይል ተዋ
ግታ ትመልስዋለች የሚል እምነት አልነበራቸውም ። ባለፉት ምዕ
ራፎች በዝርዝር እንደ ተመለከትነው ፣ ኢጣልያኖች ሕዝቡንና ባላባ
ቱን ከማዕከላዊው መንግሥት ለመለያየት የሚያደርጉትን ጥረት በጋ
ዜጣ በመስማት በኢትዮጵያ ውስጣዊ አንድነት ላይ የማይጠራጠር
አልነበረም ። ቢሆንም ሁለቱ ጠላቶች በአላጌና በመቀሌ ከተቆራ
ቆሱ ጀምሮ ለዋንኛው ለዓድዋ ጦርነት መሰለፋቸውን የሚያውቁ

መንግሥታት ሁሉ ነገሩ ይለያል በማለት በሩቅ ሲመለከቱ ቆይተው ሳይታሰብ የኢጣልያ ጦር የመሸነፉ ወሬ ሲሰማ ሁሉም በመደነቅ ባሕር ተዋጡ ። ከዚያም ቀጥሎ ባለው ጊዜ ውስጥ የኢጣልያ መንግሥት ድሉን በመበቀል ፋንታ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴውን ልኮ በውጫሌ ውል ላይ የነበረውን የጠባቂነት ምኞቱን ሁሉ ሰርዞ ፣ የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት ዐውቆ የሰላም ውል ተዋውሏል ። የዚህ ውል ግልባጭ በደንብ የደረሳቸው መንግሥታትና ሌሎችም ወሬውን ከጋዜጣ የተረዱት ሁሉ ፣ የኢትዮጵያን የተረጋገጠ መንግሥትነት በውድም በግድም ወደ ማወቅ ደረሱ ። እጠራጣሪው ነገር ሁሉ ከየተመልካቹ ልብ ተወገደና ከብዙ ዘመን ጀምሮ የኖረው የኢትዮጵያ መንግሥት አሁንም ነጻነቱን እንደያዘ በደንብና በድርጅት የሚራመድ መሆኑን ተገነዘቡ ።

ከዚህ በኋላ ፣ ሁሉም ወደዚሁ አገር መላከተኛ ለመላክ ይሽቀዳደም ጀመር ። ልዑል ሐንሪ የሚባል የኦርሊያንስ (ፈረንሳዊ) መስፍን ስለ ኢትዮጵያ ጉብኝቱ በጻፈው መጽሐፉ ላይ ፣

> ...ያለፈው ዓመት የሐበሻን ዘር የተዋጊነቱን የዠግንነቱን የኃይሉን ምስክርነት በሚያንጸባርቅ መንገድ ገልጾልናል ። በመጋቢት 1 ቀን 1896 (የካቲት 23 1888 ዓ. ም.) ከዚህ በፊት በቅኝ አገር ታሪክ ውስጥ ተደርጎ የማይታወቅ እድራጎት መፈጸሙን አየን ። አንድ የነጭ ጦር በገሃድ በተደረገ የሰልፍ ጦርነት በጥቁር ጦር ተመትቶ ፈረሰ ። ይሽም የነጭ ኃያል መንግሥት በአንድ ውል ላይ የነበረውን አንቀጽ ባጉል ተርጉሞ ለመውረር መብቱን ራሱ በወሰደበት ምክንያት ነው ። 1

ብሏል ። ሌላው ጸሐፊ ደግሞ ፤

> ከ2ሺ ዓመት በፊት ሐኒባል በሮማውያን ካገኘው ድል ወዲህ በዓለም ያንጸባረቀው የዓድዋ ድል አፍሪካ በአውሮፓ ላይ እንዳገኘው ታላቅ ድል ይቆጠራል ።" 2

ሲል በአድናቆት ጽፏል ።

ስለዚህ ፣ በኛ በኢትዮጵያውያንና በአፍሪካውያን ብርዕና እንደበት ብቻ ሳይሆን የተገኘው ድል ፣ የመላው አፍሪካ ድል መሆኑን በዘር ልዩነት የማያምኑት የአውሮፓ ጸሐፊዎች እምነውበታል ማለት ነው ። በዘር ልዩነት የሚያምኑትም ምንም የመበሸቅ ስሜት ባይስያቸው የሚያንጸባርቀውን ሐቅ ማስተባበል አይሆንላቸውም ።

1) Une Visite a l' empereur Menilik . . .,P.3.

2) Ethiopie d' Hier et d' Aujourd' hui - Andre Davy , P.106.



በዚህ ምክንያት ፣ ከዓድዋ ድል በኋላ ዳግማዊ ምኒልክ ጥቅምት 17 ቀን 1889 ዓ.ም ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ያደረጉትን የሰላም ውል ለወዳጆቻቸው ለፈረንሳይና ለመስኮብ እንደዚሁም ለእንግሊዝና ለሌሎቹም መንግሥታት በይፋ አስታወቁ ። እነዚሁ መንግሥታት የኢትዮጵያን መንግሥት ማወቃቸውን ለማረጋገጥ በማከታተል ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሮቻቸውን ከዚህ እንደሚከተለው እየላኩ የንግድና የወዳጅነት ውል መዋዋል ጀመሩ ።

ሀ. የፈረንሳይ መንግሥት ሙሴ ሌዎንስ ላጋርድን በመጋቢት ወር 1889 ዓ . ም ፣

ለ. የመስኮብ መንግሥት ሙሴ ፓ.መ..ቭላሶቭ በዚሁ ዓመት በጥር ወር ፣

ሐ. የእንግሊዝ መንግሥት ጀምስ ረኔል ሮድን በግንቦት ወር በዚሁ ዓመት ቀጥሎ ሌተና ኮሎኔል ጉርን ላን ሐሪንግተንን ፣

መ. የኢጣልያ መንግሥት መጀመሪያ ማዦር ኔራሲኒን ፣ ቀጥሎ ካፒቴን ፌዴሪኮ ቺኮዲኮላን ላኩ ። የቀሩትም እንደ ጀርመን ፣ እንደ ቤልጅክ ያሉት መንግሥታት ይሽንኑ መስመር መከተል ግዴታቸው ሆነ ። 1

መልዕክተኞቹም ከየግል መንግሥታቸው የተላኩበትን የሹመት ደብዳቤ ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርበው ሰፋፊ ቦታ እየተመሩ የየራሳቸውን የመኖሪያና የቢሮ ቤት እየሠሩ ሌጋሲዮናቸውን እያቋቋሙ ተቀመጡ ። በዚህ ጊዜ በአዲስ አበባ የሹመት ደብዳቤ ለማቅረብና ከኢትዮጵያ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ለማድረግ ከመጡት ውስጥ በወዳጅነት የሚታዩትና በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሞገስ አግኝተው መንከባከብ ያገኙት ፣ በጦርነቱ ሰዓት ኢትዮጵያን በመሣሪያም በአሳብም የረዱት የፈረንሳይና የመስኮብ መልክተኞች ናቸው ። በዚያን ሰዓት ሽር ጉድ የሚሉትም የነዚህ አገሮች ተወላጆች እነሊዎንቲቭ ፣ እነ ሞንዶን ቪዳዬ ነበሩ ። የእንግሊዝና የኢጣልያ መልክተኞች ባለፈው የጠበኛነት ሁኔታዎች ገርበብ ብለው ለመታየት ሁኔታው ያስገደዳቸው ይመስላል ።

ቢሆንም ፣ ከዕርቁ በኋላ እያንዳንዳቸው በይፋ ከመንግሥታቸው ተልከው ለመጡት የዲፕሎማቲክ አባሎች ለሁሉም ይነስ ይብዛ

1 I Russi in Etiopia, PP. 240 -279.

እንደደንቡ የክብር አቀባበልና የመንከባከብ መስተንግዶ ተደርጐላቸዋል ። የዳግማዊ ምኒልክም መንግሥት ለሁሉም የእኩልነት መልክ ከማሳየት አልተቆጠበም ።

የአቀባበሉን መጠነኛ ሥዕል ፡ የእንግሊዙ ዋና መላከተኛ ከተከታዮቹ ጋር ወዳጼ ምኒልክ በቀረበበት ሰዓት እንዳጋጣሚ በዚያው የነበረው ከዚህ በፊት ስሙን የጠቀስነው የፈረንሳይ ተወላጅ ልዑል ሐንሪ የኦርሌያንስ መስፍን ከዚህ እንደሚከተለው ያቀርብልናል ።

. . . የእንግሊዝን መልእክተኞች ለመቀበል ሲዘጋጁ ንጉሠ ነገሥቱ በአዲስ አበባ የምንገኘውን አውሮፓውያን ሁሉ ባጠገባቸው እንድንሆን ጋበዙን . . . ከቦንቫሎና ከወገኖቹ በቀር ለንጉሠ ነገሥቱ ክብር ስንል ሁላችንም ኒሻናችንን አድርገን ነበር ። ሊዎንቴቭ በኒሻን ተንቆጥቁጦ ኡኒፎርሙን ፥ ምንዶን ጥቁር ልብሱን ለብሰው ይታዩ ነበር . . . ንጉሠ ነገሥቱ ቀደም አድርገው ወደ ግል አትክልታቸው ውስጥ አስጠርተውን ነበር ። እዚያም ሆነን (ታላቁ ቤተ መንግሥት) በፊታችን ሜዳው ለጥ ብሎ ይታየን ነበርና በኮባ ጥላ ሥር ሆነን የእንግሊዞችን መላከተኞች ግራና ቀኝ ከፊትና ከኋላ ፈረሰኛና ወታደር አጅቧቸው ፈረሰኞች ከፊት ፊት ሆነው ደንገላሳ እያስነሡ ፉንጠዝያ ሲያሳዩ ይታየን ነበር . . . እጀቡ መጠጋት ሲጀምር ፥ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ መቀበያው አዳራሽ ሲገቡ እኛም አብረን ገባን ። ያጌጠው አዳራሽ ሠላሳ ሜትር ቁመት ፥ ሐያ ሜትር የሚሆን ወርድ ነበረው ። ንጉሠ ነገሥቱ የወርቀ ዘቦ አጎበር ባለው ውስጥ በከፋይ ባጌጠው ዙፋን ላይ ተቀምጠው በጥሩ ከፋይ የተከፈፈ ካባ ለብሰው ራሳቸውን በብጫ ቀለም የሐር ሻሽ አስረው ይታዩ ነበር ። በጣታቸው ላይ ከመስኮብ ንጉሠ ነገሥት ዘንድ ሊዎንቴቭ ያመጣላቸው ትልቅ ያልማዝ ቀለበት ያበራ ነበር ። በአንገታቸውና በደረታቸው ላይ የመስኮብ ከፍተኛው ኒሻንና ከፈረንሳይ የሌዥዮን ዶነር ጥላክ ጋር ባንድነት ያንጸባርቅ ነበር ። ከዙፋኑ በስተቀኝ እኛን ወዳጆቻቸውን ፈረንሳዮችንና መስኮቦችን አስቀምጠውን በግራ በኩል ትንሽራቅ ብሎ አንድ ወታደር ዘውድ የደፋና መስቀል የጨበጠ የአንበሳ ሥዕል ያሰበትን ባንዲራ ይዞ ቆሞ ነበረ ። የባንዲራው ወርቅማ ሥዕል ቅጠልማና ቀይ ቀለም ተባብሮበታል ። በርሱ አጠገብ የቤተ መንግሥቱ ታላቆች ተቀምጠው ነበር ። . . . ብዙው ጥሩ ጥሩ የሐር ልብስ የለበሰ ነው ።

ያዳራሹ ዙሪያ በጦር ሠራዊት ተመልቷል ። የጠቅላላው ሠራዊት ትርዒቱ ፥ የለበሰው ሐር ቀለሙ የተለያየ ነው ። ግማሹ በመድፉ ዠርባ ቆሞ ግማሹ ከጉማሬ ቆዳ የተሠራውን ጋሻ አንግቦ ጠበንጃውን ይዞ . . . በወርቅና በብር ያጌጠውን ልብስ በለበሱት መካከል የአራዊት ቆዳ የለበሱ ሲታዩ ዐይንን አይመታም ። ይኸውም ማለት በትከሻቸው የነብር ቆዳ የደረቡና ክንዳቸው ነጻ የሆኑት ግማሾቹ ያንበሳ ጐፈር የሰበሱ ነበሩ ።

. . . ንጉሠ ነገሥቱ እንግሊዞቹ እስኪደርሱ ድረስ እንደልባችን እየተዘዋወርን ለመመልከትና ፎቶግራፍ ለማንሣት ፈቅደውልን ነበር ።



. . . ወደ አዳራሹ በሚወስደው መንገድ ላይ 60 መድፎች ከነዚሁ ከሦስቱ አንዱ እጅ ከኢጣልያኖች የተማረኩት ተጠምደው ያሉበትን በታ እያቋረጡ አልፈው እንግሊዞቹ ሲመጡ ታዩ ።

ዋናው መሪ ሮድ የዲፕሎማት ዩኒፎርሙን እንደ ለበሰ ከሌሎቹ ቀደም ብሎ በንጉሡ ፊት ሲደርስ እጅ ነሣ ። ምኒልከም እጃቸውን ዘርግተው ጨበጡት ። ከዚህ በኋላ ከኛው ፊት በተደረደረው ወንበር ላይ እንግሊዞቹ ተቀመጡ ። በሮድ ቀኝ ኰሎኔል ዊንጌት ከርሱ ተከታትለው አንድ ግብጻዊና የሕንድ የፈረሰኛ የጦር መኮንኖች ተቀመጡ ። በነርሱ ዠርባ 8 ረዣዥም ዠርጋዶች የሕንድ ወታደሮች ራሳቸውን በሻሽ ያሰሩ በነርሱም ፊት ለፊት ሊዎንቴቭ ያመጣቸው ሁለት የኮዛክ ወታደሮች ነበሩ ። . . . ሮድ ፈረንሳይኛ ደህና አድርጎ ስለሚያውቅ በግራዝማች ዮሴፍ አስተርጓሚነት ስለጉዞው . . . ንግግር ከተለዋወጡ በኋላ ፥ ሮድ ከንግሥቲቱ የያዙት መልእክት እስ ስላለ አንድ አገልጋይ በግልጽ ስማያዊ ሐር የተሸፈነ እንደ ከረጢት ያለ አመጣለት ። በዚያን ጊዜ መላከተኛው ሁሉ ብድግ ብሎ ሲቆም ከውጭም የመድፍ ድምፅ ያስተጋባ ጀመር ። በዚህ ጊዜ ሮድ ቆሞ ‘60 ዓመት ሙሉ ለግዛቷ ሰላም በሰጠችውና ከሌሎች አገሮች ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ባደረገችው የእንግሊዝ ንግሥት የሕንድ ንግሥተ ነገሥታት ቪክቶሪያ የወዳጅነት መልከቷን ለንጉሠ ነገሥቱ አደርስ ዘንድ ታዝዣለሁ ። በሐበሻም ላይ የጠላትነት ስሜት እንደሌለን የጥንቱን የእንግሊዝንና የሐበሻን ግንኙነት እንደገና ለማደስ መፈለጋችንን አረጋግጣለሁ’ ብሎ ደብዳቤውን ሲሰጣቸው ንጉሠ ነገሥቱ ተቀብለው በጭናቸው ላይ አቆዩና አጠገባቸው ካሉት ከግብጽ ከዲቭና ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ደብዳቤዎች ጋር ደባለቁት ። ቀጥሎ የንግሥቲቱን ጤንነትና ያውሮፓን ወሬ ጠያይቀውት ካበቁ በኋላ . . . ሮድ እያንዱንዱን የመልክተኛ አባል በስሙ እየጠራ ለንጉሠ ነገሥቱ እያቀረበው ሰላምታ እየሰጠ አለፈ ። . . . ንጉሠ ነገሥቱ ከሮድ በቀር የማናቸውንም እጅ አልጨበጡም ። . . . ከዚህ በኋላ እንግዲህ ደከሟችኋልና ነገ እነጋግራችኋለሁ ብለው አሰናበቷቸው ።

የጅቡቲ (ኦቦክ) አገረ ገዥ የነበረው ሙሴ ሊዎንስ ላጋርድ በኢትዮጵያ ተቀማጭና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትርነት ተሾሞ ሲመጣ የተደረገለት አቀባበል ከሁሉ የበለጠ ነበር ። ገና ሐረር ሳይደርስ ራስ መኰንን ልጅ ቢራቱ የሚባለውን መስፍን ከ3,000 አጃቢ ጋር ልከው በረሃውን ሳይጨርስ አሳጅበውታል ። ራሳቸው 15ሺ ጦር ይዘው ኮምቦልቻ ድረስ በመሔድ በታላቅ ክብር ተቀብለውና በደስታ አስተናግደው ወደ አዲስ አበባ ሸኝተውታል ። ካፄ ምኒልክም ጋር በይፋ የተገናኘለት በታላቅ ክብርና ፍጹም በሆነ ወዳጅነት ተቃብለው ካነጋገሩት በኋላ አንገቱን በማቀፍ የደስታ ስሜታቸውን ገልጸውለታል ።[1]

1 L’ Empire des Negus, Pierre - Alype, P. 93.



ከዓድዋ ድል በኋላ የእንግሊዝ መልክተኛ አዲስ አበባ ሲገቡ
ከቤተ መንግሥት መዝገብ ቤት

## ምዕራፍ ስድሳ ሁለት

### የራስ መንገሻ ዮሐንስ መክዳትና እንኮበር መታሰር

ራስ መንገሻ ፣ የዓድዋን ጦርነት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በመሰለፍ ተዋግተው ድል ከተገኘ በኋላ ፣ በትግሬ ግዛት ንጉሠ ነገሥቱ አቋቋመዋቸው እንደዚሁም በጦርነቱ ጊዜ ለተጐዳው ሰዋቸው የሚሰጡት 30,000 የማሪያ ቲሬዛ ብር ዳረጐት ሰጥተዋቸው ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሱ ባለፉት ምዕራፎች ተዘርዝሯል ። ከዚያም ወዲህ ዝምድናው እየጠበቀ እንዲሔድ ሲባል ፣ በንጉሠ ነገሥቱና በእቴጌ ጣይቱ መልካም ፈቃድ የእቴጌን ታናሽ ወንድም የራስ ወሌን ልጅ ወይዘሮ ከፋይን ድረውላቸዋል ። ደጃች ሥዩም አባ ጐበዝ የሚባሉትንም ዋና የራስ መንገሻ ባላንጣ ራስ መንገሻን እንዳያስቸግሩ ባዬ ምኒልክ ትእዛዝ በግዞት እንዲቀመጡ ተደርጎ በጠቅላላው የራስ መንገሻ ሥልጣን በትግሬ አገር ተረጋግጦ ነበር ።

ነገር ግን ፣ ራስ መንገሻ በመተማ ጦርነት ፍጻሜ ላይ ያዬ ዮሐንስ አልጋ ወራሽነታቸው ተነግሮላቸው ስለነበረ ፣ ባዬ ምኒልክ በኩል የተደረገላቸው ሁሉ ከልብ ያስደሰታቸው አይመስልም ። “ ንጉሠ ነገሥትነቱ እንኳን ቢቀርብኝ በትግሬ ለምን አልነገሥሁም ” የሚል ቅሬታ ያላቸው ይመስላል ። ባዬ ምኒልክ ዘንድ ደግሞ የመንገሻ መገባትና መታመን ከልብ አለመሆኑን ፣ ንጉሥ ቢባሉም ባይባሉም ፣ ሲመቻቸው ከዚህ ቀደም በመረብ እንደ አደረጉት እንደሚከዱ የተገነዘቡት ይመስላል ። በዚህም ላይ በወሎም ራስ ሚካኤል ፣ በሐረርም ራስ መኰንን ንጉሥ መሆን ሳያምራቸው አልቀረም ። ነገር ግን ፣ ምኒልክ ትክለኛ ባላባትነትን ነቅለው ዕድገት ባገልግሎት ላይ ብቻ እንዲመሠረት ስላሰቡ ፣ የነጋሢነትን ደረጃ በዘመናቸው ለማንም ላለመስጠት የወሰኑ ይመስላል ።

የሆነ ሆኖ ፣ ምኒልክም ጥርጣሬያቸውን በልባቸው እንደያዙ ፣ መንገሻም የመንገሥ ፣ ይኸውም ያልሆነ እንደሆነ የመሸፈት ዓላማቸውን ደብቀው ሁለቱም በሕብረት የበላይና የበታች ፣ አባትና ልጅ መስለው በመሥራት እስካሁን ቆይተዋል ። በእቴጌ ጣይቱም በኩል የወንድሜን የራስ ወሌን ልጅ ወይዘሮ ከፋይን አግብቶ ስለ ወለደ

ዝምድናችን ጸንቷል ብለው ከመተማመን ጋር እንደ ደጃዝማች
ገብረ ሥላሴ ባሪያ ጋብር ያሉት የኛ የልብ ታማኝ አገልጋዮች ስለሆኑ ፤
በትግሬ በኩል ያለው ችግር እየተቃለለ ሒዷል የሚል ስሜት
በቤተ መንግሥቱ ያደረ ይመስላል ።

በዚህ መካከል ፤ ራስ መንገሻ በ1889 ዓ. ም. በጥቅምት ወር ላይ
እንደ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ አባባል ፤ "ጃንሆይን ናፍቄያለሁና
እንድመጣ ይፍቀዱልኝ" ብለው ቢልኩ ፤ "እሺ መልካም ነው ።
ልደትን ከኛ ጋር እንድትውል ሆነህ ና" ብለው መልስ ላኩባቸው ።
ለርሳቸው ማረፊያ የደጃች ወልዴ* ቤት ማናቸውም ታድሶ እል
ጋው ፤ እጎበሩ ፤ መጋረጃው ተዘጋጅቶ ሲጠብቃቸው በታኅሣሥ ወር
መጨረሻ ለገና ጾም መፍቻ የገሃድ ለት ገብተው በተዘጋጀላቸው
ቤት ዐርፈዋል ። የግንኙነቱን ፤ የሚጋዘውን ፤ የመስተንግዶውን ዓይነ
ትና መጠን ፤ ወደ ግቢ ሲመላለሱ የግብሯውን፣ የሽልማቱንም ዓይነ
ትና ብዛቱን ከተረኩ በኋላ የክዳቱን ሰበብ ጸሐፌ ትእዛዙ ሲያወሱ ፤ እን
ደርታ የባላገር ልጅ ተሰፋዬ የሚባል ያዩ ዮሐንስ የልፍኝ አስከል
ካይ የነበረ በአሁኑ ጊዜ የራስ መንገሻ አሽከር ሆኖ እንደሚያገለ
ግል ፤ ስለዚህም ራስ መንገሻ ፤ ራስ ስብሐትን አስረው ተሰፋዬን
ሹም አጋሜ ብለው እንደ ሾሙት ፤ ሌላ ደግሞ ባሻ ተወልዱ
የሚባለው እነዚህ ሁለቱ ራስ መንገሻን እንግሥው ተሰፋዬ ራስ
ለመባል ፤ ተወልዱ ቱርክ ባሻ ለመሆን እንዳነሣሡዋቸው ፊትም እናን
ግሥሃለን ብለው ለኢጣልያ ያስገቡዋቸው** እነዚህ መሆናቸውንና
ራስ መንገሻ ግን ሰውነታቸው ጸጥ ያለና የረጉ ናቸው በማለት መዝግ
በውት ይገኛል ።[1]

ከዚሁ እያይዘው ይኸው ባሻ ተወልዱ ወደ አቡነም ፤ ወደ እጨ
ጌም ፤ ወደየመኳንንቱም እየዞረ ፤ "የመጣነው ሊያነግሡን ነው ። ጌታ
ችንን መቼ ነው የሚያነግሡልን" እያለ ማውራቱን ፤ የዚህንም ወሬ
እቴጌ ጣይቱ ሰምተው ማዘናቸውን ፤ ከዚያም እቴጌ ሹም አጋሜ ተሰ
ፋዬን አስጠርተው ፤ "ምንድነው እንደዚህ እያላችሁ ታወራላችሁ"
ብለው ቢጠይቁት እንዳልሰማና እንዳልመከረ ሁሉ ፤ " እልሰማሁም
ግን አሰበውና" የሚል መልስ መስጠቱን ፤ ከዚያ ተሰፋዬ ወደ ራስ
መንገሻ ሔዶ "እንነግሣለን ብላችሁ ታወራላችሁ . . . በማናቸው
አገር ትነግሣላችሁ መንግሥት እንደዚህ ዋዛ ነው" ብለው እቴጌ

* በኋላ ራስ የተባሉት የደጃች መሸሻ አባት ።
** መረብ ከጄኔራል ጋንዶልፊ የተቀዋሉትን ሲጠቅሱ ነው ።
1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . . ምዕ. 65 ገጽ 272-274



ተቆጡኝ ብሎ ለራስ መንገሻ መንገሩን ፤ ራስ መንገሻም በልባቸው
ተቆጥተው ከነተሰፋዬ ጋር ሲመካከሩ አድረው በግለጻ እንደወጡ
ወደ እቴጌ ዘንድ መጥተው ፤ "ትላንትና ሹም አጋሜ ተሰፋዬ የእቴ
ጌን ቁጣ ነገረኝ ። እኔም እጅግ አድርጌ አዘንሁ ። እኔ ዘበኛ በር ጠባቂ
ነኝ ። የሚመጣውን ነገር ሁሉ ለናንተ ልነግር መጣሁ እንጂ እነግ
ሣለሁ ብዬ አልመጣሁም . . . ደግሞስ እግዚአብሔር የሚያነግሠኝ
ከሆነ ያለሁበት ቦታ ጠፍቶት ነውን ለየመኳንንቱ የምነግሠው
መቼ ነው እያልሁ የምጠይቀው" ብለው በቁጣ ቃል መናገራቸ
ውን ፤ እቴጌይቱም ለዚህ መልስ . . . ንጉሥ እንዲህ ሲወዱህ ሲያ
ፈቅሩህ ይህንን የሰሙ እንደሆን ይቀየሙብሃል ፤ ሰውም ያነውርሃል ብዬ
ነው እንዲህ መናገሬ ። አንተ የጥንት የጌታ ልጅ ነህ ፤ ፊትም እያ
ትህ ስሑል ሚካኤል* ራስ ተብለው ነው የገዙ . . . ራስ ወልደ
ሥላሴም ራስ ተብለው ገዙ ። የኛም አባት ደጃች ውቤ** ከምጥዋ
እስከ ባምብሎ ድረስ ደጃዝማች ተብለው ገዙ ። "አንተ ዛሬ መንግሥት
(መንገሥ) ምን አሳሰበህ . . ." ብለው ቢመከሩአቸውም ፤ ምክሩ
ለመንገሥ የተነሣውን ምኞታቸውን ሲያበርድ አልቻለም ።

ስለዚህ ከአዲስ አበባ ተሰናብተው ቅርታቸውንና ለመሸፈት
ማሰባቸውን ሳይገልጡ ከንጉሠ ነገሥቱ ፤ ከእቴጌይቱም ተሰነባብተው
ወደ መቀሌ እንደ ተመለሱ መሸፈታቸው ተሰማ ። ቢጠሩም " እኔ ለዘ
መቻ የሚሆን ባይሆን ወታደር አልካለሁ እንጂ ራሴ አልመጣም"
ብለው ስለላኩ መሸፈታቸው በእርግጥ ታወቀ ። ዐፄ ምኒልክ በተለ
መደ ትዕግሥታቸው ወዲያው ጦር ልከው ፤ " ሒድ ውጋው ፤ ግር
ከው ፤ ግደለው" ሳይሉ አባብለው የሚያስገቡበትን በዘመኑ በኢትዮ
ጵያ የተከበሩትን አበውና አረጋውያን መምህር ዜናን ፤ መምህር ፈቃ
ደን ፤ መምህር አካለ ወልድን ፤ የሐይቁን መምህር አባ ዓምደ ሥላሴን ፤
የግሸኑን ግራ ጌታ ውቤንና አባ ወልደ ገብርኤልን መስቀል አስይ
ዘው በመላክ ፤ "የትግሬን አድባራት ሁሉ ይዛችሁ እኔ በድየህ እን
ደሆነ ማረኝ ፤ ይቅር በለኝ ብላችሁ መስቀሉን ተሸክማችሁ ውደቁና
አስታርቁኝ" ብለው ላኩ ። እቴጌ ጣይቱም ለብቻ ብዙ የማባበያ ቃል
ጨምረው " ልጄ ስለ መድኃኔ ዓለም ፤ ስለ ተሰቀለው ጌታ . . .

* ኢያትህ ያሉት የሩቅ ዝምድና ቀጠራ ነው እንጂ የሩቁ ራስ ስሑል ሚካኤል
ለራስ መንገሻ የእናታቸውም ያባታቸውም አባት አይደሉም ። በራስ ስሑል
ሚካኤልና በራስ መንገሻ ማሕል 6 ዘር ይወርዳል ።
** ይኸውም እንደዚያው እንደ ራስ ስሑል ሚካኤል ፤ ውቤ ለእቴጌ ጣይቱ አጎት
ናቸው እንጂ አባት አይደሉም ።

እማጥኜሃለሁ ፣ ይህን ክፉ አሳብህን ተው ፣ የሰይጣናትን ክንፋቸውን ሰበረው . . .” የሚል ቃል ጨማምረው ቢልኩ ራስ መንገሻ አንድ ጊዜ ቆርጠው የተነሡበት ጉዳይ ስለሆነ ፣ የመነኮሳቱም ልመና የእቴጌም መማጠን በዚህ ጊዜ አልሠራም ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ራስ መኰንንን ከሐረር አስጠርተው ሐረርን እንደያዙ በትግሬ ላይ ሾሟቸው ። ይኸው በዐዋጅ ተነገረና መኰንን ከአዲስ አበባ ወደ ትግሬ እንዲሔዱ ታዘዙ ። የወሎውም ራስ ሚካኤል ራስ መኰንንን እንዲረዱ ታዘዙ ። ለትግሬም ሕዝብ ቀጥሎ ያለው ዐዋጅ ተነገረ ።

> ስማ የትግሬ ሰው ፤ ራስ መንገሻ ፊት ደጃዝማች ሥዩምን አስሬ እሱን ብሾመው ከዳኝ ። አሁን ደግሞ እሾሁን ነቅዬ * አደላድየው ሾሜው ብመጣ እኔን አባቱን ከዳኝ ። የትግሬ ሰው አድባራቱም መኳንንቱም ራስ መንገሻን ሰወደው ጠልቶኛልና ግፌን እይልኝ ። እኔ ግን ፣ ያፄ ዮሐንስን ወረታ እመልሳለሁ ብዬ መኳንንትና ወታደር ሳይወደው በግድ ሾሜው ነበርና መሬት አሰናበተችው እንጂ እኔ በድየው አይደለም ። አሁንም የትግሬ ሰው ራስ መንገሻ ከዳኝ ብዬ በሱ ተናድጄ አላጠፋሁም ። እግዚአብሔር የሰጠኝን አገሬን (ትግሬን) በጄ አድርጌ አለማዋለሁ ። ደስ አሰኝሀለሁ ። አይዞህ ግባ በየአባትህ እተክልሃለሁ ። አባትህን መርቅ ፤ አባትህን እርገም ፤ ልብህ ያሰበውን የሚያደርግልህን ለባሕርይህ የሚስማማህን ልጄን ወዳጄን ራስ መኰንንን ሰጥቸሃለሁ ። ከሐረር ጋራ ትግሬን ማድረጌ አንተን እንዲያለማህ ፣ አንተን እንዲጠቅምህ ብዬ ነው ። የሱን ይሰጣችኋል እንጂ ከትግሬ የሚፈልገው ነገር የለም ።[1]

የራስ መንገሻን አሸፋፈት መኳንንቱም ፣ መሳፍንቱም ያወገዙት ይመስላል ። ስለዚህ ጉዳይ ንጉሠ ነገሥቱ ለጻፉላቸው መልስ የጐጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጥቅምት 17 ቀን 1892 ዓ. ም. በጻፉት ደብዳቤ እንደዚህ ብለዋል ።

> ኃበ ሥዩመ እግዚአብሔር ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። ጃንሆይ የራስ መንገሻን ነገር እዚያው አዲስ አበባ ሳለሁ ሁሉንም አመልክቼዎ ነበር ። የርሱም ነገር የቀረው ሁሉ ምሕረትዎ ትዕግሥትዎ ቀርቶ ፊት ደጃዝማች ሥዩምን አስረው የሰጡት ፣ ኋላም ድፍን አበሻን አስከትለው ዘምተው ከጠላታችን ከኢጣልያ ተዋግተው ሠራዊትዎን አስፈጅተው እርሱን ሾመው ለቁስለኛው መዳኛ ለሠራዊቱ ደመወዝ ሰጥተው የመጡት ውለታዎ አይበቃም ነበር . . . አሁንም ሰውን አስፈጅቶ እሱ አራት አምስት ሆኖ ቢወጣ

* እሾሁን ነቅዬ የሚሉት ሥዩም አባ ጉበዝን ሽረው የሰጧቸውን ለማውሳት ወይም ጣልያንን በድል መልሼ ለማለት ይሆን ?

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ገጽ 291



> ምን መውጣት (መሸፈት) ነው ። አሁንም የኃጢአት ውዝፍ ይኖረዋል ። ያንን ጨርሶ ከእጅዎ ይወድቃል እንጂ መውጣቱ ሊሰነብት አይደለም ።[1]

ራስ መንገሻ ፣ በዚህ አያያዝ ሲሸፍቱ አስታራቂም እምቢ ሲሉ ምኞታቸውን ከአቅማቸው ጋር ማመዛዘን የተሳናቸው ይመስላል ። ያለፈውንም ያፄ ዮሐንስንና የንጉሥ ምኒልክን የግንኙነት ታሪክ በደንብ አጢነው ከራሳቸው አቅዋም ጋር አላመዛዘኑትም ።

ከዓድዋ ድል በኋላ ፣ ያፄ ምኒልክ መንግሥት በጣም መደርጀቱን እየተገነዘቡትና ጣሊያኖችም ፣ እንግሊዞችም ፣ ሌላም መንግሥት በዚህ ጊዜ በፍጹም ሊረዳቸው የሚችል እንደሌለ እያወቁት ፣ ያንያህል የልመና ብዛት ሲወርድላቸው ልባቸው በሽፍትነት የጠጠረበት ምክንያት ከዚህ ራቅ ካለው ዘመን ላይ ሊገባን አይችልም ። ከመረቡ ስምምነት ወዲህ ከአመዛዛኙና ከታወቁት አርበኛ ከራስ አሉላ ጋር ያጣላቸውም ይኸው አጉል አቅዋማቸው ነው ። የበታች መሸፈቱንም ፣ መገዛቱንም ያላወቀበት እንደሆነ ለበላዩ ችግር ይፈጥራል ። በደካማ አቅም ኃይለኛን መግጠምና ሰውን በከንቱ ማስጨረስ ፋይዳ የሌለው መሆኑ ግልጽ ነው ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ ከራስ መኰንን ጋር ራስ ሚካኤልን ፣ ዋግሹም ጓንጉልን ፣ ደጃዝማች አባተን አድርገው ወደ ትግሬ ሲልኩ ፣ “ ዐውቆ እጁን ቢሰጥ ይዛችሁት ኑ ፤ እምቢ ካለ ውጉት ” ብለው መመሪያ ከሰጡ ወዲህ ከሸዋም የሔዱት ራስ መኰንንና ደጃች አባተ ከዋግሹም ጓንጉልና ከራስ ሚካኤል ጋር ተገናኝተው ወደ መቀሌ ሲጓዙ ራስ መንገሻ መቀሌን ለቀው ኢጣልያኖች ከዓድዋ ጦርነት ቀደም ብለው መሽገውበት ወደ ነበረው ወደ እዳጋ ሐሙስ ሔደው በዚያ ለመከላከል አሰቡ ። በዚያም ሳሉ ፣ ከራስ መኰንንም ከራስ ሚካኤልም እንዲገቡ የምክር ቃል ተልኮ ስለአልገቡ በጀርባ በአጋሜ በኩል 4000 ባለ ጠበንጃ ዘልቆ በተደረገው ጦርነት የራስ መንገሻ ጦር ክፉኛ ተጐዳ ። ከዚህ በኋላ ፣ ራስ መንገሻ “ ትግሬን አገርዎን ለወደዱት ይሹሙበት እኔን ለእጄ አስምሩኝ” ብለው እጃቸውን ለራስ መኰንን ሰጡ ። በዚህም ጊዜ ቀድሞ የአጋሜን ሹመት ለተስፋዬ ሰጥተው አስረዋቸው የነበሩትን ራስ ስብሐትን በአጋሜ መልሰው ሾመዋቸው ከርሳቸው ጋር አስተባብረዋቸው

1 ከታላቁ ቤተ መንግሥት የቀድሞ የጽሕፈት ሚኒስቴር መዝገብ ቤት ቁ. 42 ተመዝግቦ የተገኘ ።

ነበረና እርሳቸውም በዚህ ቀን አብረው ለራስ መኰንን እጃቸውን ሰጡ ።

ዐፄ ምኒልክም ፣ ከአዲስ አበባ መጥተው ወሎ ላይ ሆነው ሁኔታውን ይጠባበቁ ነበር ። ራስ መኰንን ላስተዳደር መቀሌ ሲቀሩ ፣ ራስ ሚካኤል እስረኞቹን እንደያዙ መጥተው በየካቲት ወር መዠመሪያ ላይ 1892 ዓ.ም. ወረይሉ ገቡ ። መንገሻም ፣ ስብሐትም እንደ ኢትዮጵያ ልማድ ደንጊያ ተሸክመው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ወድቀው ምሕረት ለመኑ ። ሁለቱም በጠባቂ ሆነው አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ፣ አንዱን ዓመት እንደ ቁም እስር ሆነው በአዲስ አበባ ቆዩ ። በእቴጌይቱ አማላጅነት ራስ ስብሐት አጋሜን አገራቸውን አስመርቀው ወደ አዲግራት ሲመለሱ ፣ ራስ መንገሻ "እጃቸውን ቢሰጡም ልጆቻቸውን ደጃዝማች ሥዩምንና ደጃዝማች ጉግሣ አርአያን በትግሬ አስቀርተው አሁንም እየተላላኩ አሸፍተዋል" ተብለው ተወቅሰው አንድ ዓመት ያህል በደንዲ ደሴት ታሰሩ ። ከዚያ በ1894 ዓ.ም. ወደ አንኮበር ተዛውረው በአዛዥ ወልደ ጻድቅ እጅ ታስረው ሲኖሩ በጥር ወር 1898 ዓ.ም. አንኮበር ሞቱ ።[1]

ራስ መንገሻ ፣ በአንኮበር በጉብታው ላይ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቤተ መንግሥት በጠባቂ ሲኖሩ ፣ አገረ ገዥው ወህኒ አዛዥ ወልደ ጻድቅ ወደማታ እየሔዱና አደግድገው እየገቡ አብረው ራት እየበሉ ሲያጫውቷቸው አምሽተው ወደ ቤታቸው ይመለሱ እንደነበረ ፣ ጠያቂም ከየአለበት ሲመጣ በወህኒ አዛዡ ፈቃድ እየገባ ራስ መንገሻን ያጫውታቸው እንደነበረ ፣ ያዛዥ ወልደ ጻድቅ አሽከር የነበረ ሽማግሌ አንኮበርን በጎበኘንበት ቀን ለደራሲውና ለደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ አጫውተውናል ። ከሽማግሌው ከተለያየን በኋላ ደጃዝማች ዘውዴ "ይገርማል በትግሬ አገር የሚወራው መንገሻ በአንኮበር በእግረ ሙቅ በጥብቅ ታስረው ሕዝቡ በዙሪያቸው እንዳይደርስ ተናካሽ እባብ በዙሪያቸው ተደርጎባቸው ግራ ቀኝ ሲነቃነቁ ይነከሳቸው ነበር" የሚል ነው ብለው በነገሩ አሳዛኝነት ሁለታችንም መገረማችንን ደራሲው ያስታውሳል ።

---

* ደንዲ ከአምቦ በስተደቡብ የሚገኝ ደሴት ነው ።

1 Maurice de Coppet, Chronique du Regne De Menelik II, vol. II, PP. 471-483, 620, 621 Annaratore, in Abyssinia, PP. 60-63.



# ምዕራፍ ስድሳ ሦስት

## ከውጭ መንግሥታት ጋር የተደረጉት ውሎች

## የሦስቱ መንግሥታት የክፍፍል ስምምነት

ከዓድዋ ድል በኋላ ፣ ኢጣልያ በውጫሌ ውል የተነሣ ተመኝታ የነበረውን የበላይነት ጉዳይ ሰርዛ ከኢትዮጵያ ጋር በይፋ በእኩል መንግሥትነት ደረጃ እ.ኤ.አ.በ1897 ዓ.ም. የወዳጅነት ውል ካደረገች ወዲህ ፣ የውጭ መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ የነበራቸውን የንቀትና የማወላወል ሁኔታ ወደጐን አድርገዋል ። ከዓድዋ በፊት ኢጣልያን ይደግፍ የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት ሳይቀር መልክተኞቹን ልኮ ከኢትዮጵያ ጋር መልካም ግንኙነት ለማድረግ ተገደደ ። ወዲያው በዚሁ ዓመት ሌጋሲዮኑን በኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብአዲስ አበባ ከከፈተ ወዲህ ፣ እ.ኤ.አ. በግንቦት 14 ቀን 1897 በ6 አንቀጾች የተከፈለ የወዳጅነት ስምምነት ፣ እንደዚሁም በዘይላና በሌሎችም የእንግሊዝ ቅኝ አገሮችና በኢትዮጵያ መካከል ስላለው የወሰን ክልል ፣ ስለ ጸጥታ ፣ ስለ ቀረጥና ስለ ጦር መሣሪያ መተላለፍ ጉዳይ ደንበኛ ውል ተዋዋለ ። ቀጥሎ በ15 ግንቦት 1902 ዓ. ም. እ.ኤ.አ. በሱዳን በኩል ስላለው ወሰን ፣ ስለ አባይና ስለ ጁባ የወንዝ ፈሳሾች ጉዳይ በ5 አንቀጾች የተከፈለ ውል በተጨማሪ ተዋዋሉ ።

የፈረንሳይ መንግሥት ፣ በዚሁ በ1897 ዓ.ም በመጋቢት 20 ቀን ስለ ወሰንና ስለ አሰል (አውሳ) ጨው አወጣጥ ጉዳይ ከተዋዋሉ ወዲህ እ.ኤ.አ. በ1909 ዓ.ም. በጥር ወር ጅቡቲን ስለሚያዋስነው ጉዳይና በዚያም በኩል ስለሚገባውና ስለሚወጣው ሸቀጥ ፣ ስለሁለቱ አገሮች ዜጎች አጠባበቅና መብት ፣ ስለ ንግድ ልውውጥ ፣ ስለ ጦር መሣሪያም በ9 አንቀጽ የተከፈለ ደንበኛ ውል አደረገ ።

በዚሁ ዐይነት ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት በሩቁና በቸልታ ይመለከት የነበረው የአሜሪካ መንግሥት ወኪሉን ሚስተር ሮበርት ስኪነርን ልኮ በ1903 ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር በ7 አንቀጽ የተከፈለ ስለ አሜሪካንና ስለ ኢትዮጵያ ዜጎች በየአገራቸው በነጻ ለመዘዋወር ስለሚችሉበት ጉዳይ ፣ ስለ ንግድ ፣ ስለ ወኪል ልውውጥና በጠቅላላው ስለ ወዳጅነት ውል ተዋዋለ ።

በዓድዋ ጦርነት አካባቢ የጀርመን መንግሥት ፍጹም የኢጣልያ ወዳጅ ነበረ ። በመቀሌው ጦርነት ለተዋጋው ለኮሎኔል ጆሴፔ ጋልያኖ የኒሻን ሽልማትም መላኩን እናስታውሳለን ። የዓድዋ ድል ወሬው እንደ ተሰማ ከብስጭት ላይ የወደቀውን ንጉሡን ኡምቤርቶን ለማጽናናት ከበርሊን ወደ ሮማ እስከ መጓዝ የደረሰው፣ የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ዊልሄልም አሁን ከዓድዋ ድል በኋላ ፣ የኢጣልያ መንግሥትና ሌሎቹም እየተሽቀዳደሙ ከምኒልክ ጋር በውል ሲወዳጁ እርሱ ወደኋላ መቅረት አልፈለገም ።

ስለዚህ ፍሬደሪክ ሮዘን የሚባለውን ባለሙሉ ሥልጣን ወኪል አድርጎ ወደ አዲስ አበባ በመላክ እ.ኤ.አ. በመጋቢት 7 ቀን 1905 ዓ.ም. በ6 በተከፈለ አንቀጽ ሌሎቹ መንግሥታት እንዳደረጉት የመሰለ የወዳጅነት ፣ የመቀራረብ ፣ የንግድ ልውውጥንና የዜጎች መብትን በሚመለከት ተዋውሎ ተፈራረመ ። የጀርመንንም አርአያ በመከተል የአውስትሮ — ሐንጋሪ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ፍራንሷ ዮሴፍ ሙሴ ሎዊ ሆህኔል የሚባለውን ባለሙሉ ሥልጣን ወኪል ልኮ ከጀርመን መንግሥት ጋር ከተደረገው ስምምነት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ውል በመጋቢት 21 ቀን 1905 ዓ.ም. ተዋዋለ ። ከነዚህም በኋላ የቤልዥክ ንጉሥ ሙሴ ሄኒን ሀ የሚባለውን ልኮ ተዋዋለ ።[1]

ከነዚህ ሁሉ ሦስቱ ኃያላን እንግሊዝ ፣ ፈረንሳይና ኢጣልያ በቅኝ አገሮቻቸው አማካይነት ከኢትዮጵያ ጋር ስለሚዋሰኑ ፣ በልዩ ልዩ መንገድ በኢትዮጵያ ሀብት በየበኩላቸው ለመጠቀም በቀጥታ ም በጐንም ፣ በሐቅም በተንኮልም ብዙ የሚሸርቡት መንገድ እንደነበረ የታወቀ ነው ። የዓድዋ ድል የነጭን የዘር ክብር በመንካቱ ፣ ቅርታን በመፍጠሩ ጐን ፣ ወሬው በየቅኝ አገሩ ሕዝብ መሠራጨቱ ለየትኛውም የአውሮፓ ኃያል አላስደሰተም ። በዚህም ላይ ባሁኑ ጊዜ የምኒልክ መንግሥት የሥልጣኔ ሥራ አገማመር በመጠኑ ከሥጋት ላይ መጣሉ የታወቀ ነው ። ምክንያቱም አንድ የሠለጠነ ሕዝብ በምንም ዐይነት በሌላው መገዛትን አይቀበልም ። በአሁኑ ጊዜ የአውሮፓ ገዥነት የሌሎቹ ተገዥነት መሠረታዊ ሰበቡ የሥልጣኔ ልዩነት መሆኑ ግልጽ ነው ። አንድ እንደ ኢትዮጵያ ያለ አፍሪካዊ አገር መሠልጠኑንም ፣ በጦር ኃይል መደራጀቱንም ሁሉም አይወዱትም ፤ አይቀበሉትም ።

ስለዚህ ፣ እነዚህ ሦስት ኃያላን ሲዞያዩ ቆይተው ፣ እርስ በርሳቸውም የተስማሙበትን ፣ ከኢትዮጵያ ጋር የተዋዋሉትንም ውል

1 L'Ethiopie et les convoitses allemandes, P. Alype, PP. 121-227; Storia Diplomatica dell, Etiopia . . . C. Rossetti, PP. 221 - 222, 225, 239, 291- 293.



የሚያጠቃልል በሎንዶን ከተማ የሦስቱ መንግሥታት ወኪሎች ስለ እንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኤድዋርድ ግሬይ ፣ ስለ ፈረንሳይ አምባሳደሩ ሙሴ ፖል ጋምቦን ፣ ስለ ኢጣልያ አምባሳደር ሲኞር ዲ ዡሊያኖ ፣ "የሦስቱ መንግሥታት ስምምነት" ተብሎ የሚጠራውን የከፍፍል ስምምነት እ.ኤ.አ. ታኅሣሥ 13 ቀን 1906 ዓ.ም. ተዋዋሉ ።

የመዠመሪያው አንቀጽ ሦስቱ ተዋዋዮች ፣ ኢትዮጵያ እስካሁን ያደረጋቻቸውን ውሎች በማክበር የኢትዮጵያን የፖለቲካና የወሰን ግዛት ለማክበር መስማማታቸውን ፤

በሁለተኛው አንቀጽ ፣ እነዚሁ ኃያላን ከኢትዮጵያ በሚያገኙት የንግድ ፣ የኢንዱስትሪና የእርሻ ውል በምንም ዓይነት አንዱ የሌላውን ጥቅም የሚፃረር ሥራ እንዳይሠራ ለየወኪሎቻቸው መመሪያ እንደሚሰጡ ፣

በሦስተኛው አንቀጽ ፣ ባገር ውስጥ የርስ በርስ ጠብና የባለሥልጣን ልውውጥ ቢደረግ ሦስቱም ኃያላን የገለልተኛነት አቋም እንደሚወስዱ እንጂ ፣ ባገር ውስጥ ጉዳይ እንዳይገቡ ቃል መግባታቸውን ፤ ነገር ግን የየግል ጥቅማቸውን እንደዚሁም የሌጋሲዮን ሠራተኞቻቸውንና የዜጎቻቸውን ሕይወት ለመጠበቅ እርምጃ ለመውሰድ መስማማታቸውንና በነገሩም ሊገባ የሚፈልገው ኃያል አስቀድሞ ከሁለቱ ኃያላን ጓደኞቹ ጋር ከተስማማ በኋላ መሆን እንዳለበት ።

በአራተኛው አንቀጽ ፣ ምናልባት የኢትጵያን ነጻነትና አንድነት የሚሽር ከውጭ አንድ ኃይል ቢመጣ ሦስቱ ኃያላን በመዠመሪያው አንቀጽ እንደ ተጻፈው ፣ "የኢትዮጵያን አንድነትና ነጻነት ለማስጠበቅ" ግዴታ መግባታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ፤

ሀ/ እንግሊዝና ግብፅ ፣ በአባይ ወንዝ ስላላቸው የፈሳሽ ወሃ አከፋፈል ጉዳይ . . .

ለ/ ኢጣልያ ፣ በኤርትራና በሱማሌ በኩል ስለአላት ቅኝ አገር ፣

ሐ/ ፈረንሳይ ፣ የጅቡቲ ቅኝ አገር ግዛቷና ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ የሚዘረጋውን የባቡር ሐዲድ መስመር የሚጠበቅበትን ፤

በአምስተኛው አንቀጽ ፤ የፈረንሳይ መንግሥት እ.ኤ.አ መጋቢት 9 ቀን 1904 ዓ. ም. በኢትዮጵያና በፈረንሳይ መካከል ስለ ምድር ባቡር መዘርጋት ያደረገውን ውል ለሁለቱ ኃያላን እንደሚያስታውቅ ፣ እንደዚሁም በነሐሴ 8 ቀን 1904 ከድሬዳዋ እስከ አዲስ

አበባ ስለሚራዘመው የሐዲድ መስመር ካፄ ምኒልክ የተሰጠውን የፈቃድ ውል ለሦስቱ ኃያላን እንደሚያስታውቅ ።

በስድስተኛው አንቀጽ ፥ የባቡሩ ሐዲድ ከአዲስ አበባ እስከ ድሬዳዋ ፥ ከድሬዳዋ እስከ አዲስ አበባ እንዲራዘም ምናልባትም ከድሬዳዋ ወደ ሐረርም ቅርንጫፉ እንዲዘረጋ መስማማታቸውንና በነዚህም የሐዲድ መስመሮች የሦስቱ አገሮች ሸቀጦችና ዕቃዎች በጅቡቲ ሲተላለፉ ቀረጥ እንዳይጠየቁ ።

በሰባተኛው አንቀጽ ፥ ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ስለ ተዘረጋው ባቡር አስተዳደር በማኀበሩ ውስጥ የእንግሊዝ ፥ የኢጣልያና የኢትዮጵያ መንግሥት ተካፋይ የሚሆኑበት . . . .በእንግሊዝና በኢጣልያ የባቡር ወደቦች የፈረንሳይና የኢትዮጵያ ሸቀጥ በነጻ የሚያልፍበት ፤

በስምንተኛው አንቀጽ ከዚህ በፊት ለእንግሊዝ ስለተሰጠው ውል የፈረንሳይ መንግሥት በምንም ዓይነት እንደማይገባ ፤

በዘጠነኛው አንቀጽ ከአዲስ አበባ ወደ ምዕራብ የሚዘልቅ የባቡር መስመር ለመዘርጋት የውጭ መንግሥት ተባባሪነት ቢያስፈልግም ተፈጻሚነቱ በእንግሊዝ የበላይነት ጥበቃ መሆን እንዳለበት ፤ በዚሁ መሠረት ፥ ከእንግሊዝ ሱማሌ በኢትዮጵያ ግዛት አልፎ ወደ ሱዳን የሚዘልቅ የሐዲድ መስመር ለመዘርጋት ካፄ ምኒልክ በነሐሴ 28 ቀን 1904 ዓ.ም. ቢፈቀድም ፥ በቅድሚያ የፈረንሳይንና የኢጣልያን መንግሥታት ስምምነት እንደሚያስፈልግ ፤ በኢትዮጵያ ስለሚዘረጋው ሐዲድ አስቀድሞ ካልተፈቀደ በቀር ተፎካካሪ የሚሆን ሌላ መስመር ላለመዘርጋት ሦስቱም እንደ ተስማሙ ።

በዐሥረኛው አንቀጽ ፥ ሦስቱ ኃያላን መንግሥታት እርስ በርሳቸው በግልጽ እየተወያዩ የየግል ጥቅማቸውን እንደሚጠብቁና በሦስቱ መካከል አለመስማማት ቢፈጠር ኃላፊዎቹ የዠመሩትን ሥራ አቁመው ሁኔታውን ለየመንግሥታቸው ማስታወቅ እንዳለባቸው ፤

በዐሥራ አንደኛው አንቀጽ ፥ በአንደኛውና በአምስተኛው አንቀጽ ከተባለው ውጭ በኢትዮጵያ መሬት ውል ቢወሰድም የተጠቀሱትን ሁለት አንቀጾች ስምምነት የሚፃረር እንደማይሆን ።[1]

ይህ የሦስቱ ኃያላን ውል በ1884—85 ዓ.ም. በርሊን ከተማ በርክት ያሉት የአውሮፓ የቅኝ አገር ያላቸው ኃያላን እርስ በእርሳቸው በሰላም አፍሪካን ለመከፋፈል ካደረጉት ስምምነት ጋር

1 Storia Diplomatica . . . PP. 319-325.



ብዙም ልዩነት ያለው አይመስልም ። በበርሊን ማንም አፍሪካዊ በራሱ ጉዳይ ያልተካፈለበትን አፍሪካን በሰላም ያለጠብና ያለፉክክር ለመከፋፈል ተዋዋሉ ። አሁንም ባለፈው ክዓድዋ ጦርነት ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ እንግሊዝ የፈረንሳይን ይዞታ በመቃወም ፥ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ እንድትስፋፋ ስትደግፍ ነበር ። ኢጣልያም "ኢትዮጵያን ለመውረርና በሥልጣኔ ሥር አውላታለሁ ብዬ ለተነሣሁባት ለኢትዮጵያ ከመስኮብ ጋር በመተባበር መሣሪያ እያቀበለች በፖለቲካና በሞራል እየደገፈች አስቸገረችን" ብላ ፈረንሳይን ትወቅስና ትከስ የነበረው ፥ በዚህ ጊዜ ሁሉም ወደጐን ተደርጓል ። ፈረንሳይም በእርግጥ እስከ ዓድዋ ፍጻሜ ድረስ የነበራትን አቋም ትታ ኢትዮጵያን ወደጐን ገሸሽ በማድረግ ፥ ሦስቱ የቅኝ አገር ኃያላን ላፄ ምኒልክ ሳያማክሩ የኢትዮጵያ ወኪል በሌለበት የኢትዮጵያን ሀብትና ፈሳሽ ወንዝ ያለጠብ ለመከፋፈል ያለፈውን የርስ በርስ ፉክክራቸውን የሚደመድም ይኸን የመሰለ ውል አደረጉ ።

በመዠመሪያው አንቀጽ ላይ ፥ የኢትዮጵያን ግዛት ፥ አንድነትና ነጻነት ለማክበርና ፥ በውስጥ ጉዳይም ላለመግባት ምንም እንኳን ቃል ቢገቡ ፥ ይኸ ሁሉ የባቡር መስመር በነርሱ ወጭና ቁጥጥር ውስጥ በያለበት በሚሠራጭበት ጊዜ ፥ "ጥቅማችንን ፥ የዜጐቻችንን ሕይወትና መብት እንጠብቃለን" ሲሉ ፥ ከኢትዮጵያውያን ባለሥልጣኖች ጋር ጠቡ የማይቀር ነው ። በጠቡ ሰበብ ውሉ አድሮም በትክክል ማስተዳደር አልቻላችሁም ፥ ከኛ ጋር አልተዋሐዳችሁምና በኛ ሥልጣን ተዳደሩ ማለታቸው የማይቀር ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፥ በታኅሣሥ 13 ቀን 1906 ዓ.ም. ሎንዶን ላይ ያደረጉት ይኸ የስምምነት ትክክለኛ ግልባጭ በሐምሌ ወር ላይ አዲስ አበባ በሚቀመጡት ወኪሎቻቸው አማካይነት ለንጉሠ ነገሥቱ ላፄ ምኒልክ ቀረበ ። እርሳቸውም ከወገኖቻቸው ጋር መክረው ዘከረው እንደዚህ ሲሉ መለሱ ። " . . .የሦስቱ መንግሥታት ስምምነት ደርሶኝ ተመለከትሁት ። የኢትዮጵያን ነጻነት እንጠብቃለን በሚለው በመዠመሪያው አንቀጽ ደስ ብሎኛል ፤ አመሰግናለሁ ። ስለቀረው መንግሥቴን ስለሚመለከተው ጉዳይ ኃያላኑ በራሳችሁ በተስማማችሁበት ውል የኔ መንግሥት የሚገደድበት ውል የለም ።" ይኸውም ማለት የኢትዮጵያን ጉዳይ የኢትዮጵያ ወኪል በሌለበት ብቻችሁን በተስማማችሁበት ጉዳይ እኛን ሊያስገድደን የሚችል የለም ማለት ነው ። መልሱም የተሰጠው እንደ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በኅዳር 25 ቀን 1899 ዓ.ም. መሆኑ ተመዝግቧል ።[1]

በዚህ ዓይነት ፥ የሦስቱ መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባለሥልጣኖች ሲወያዩበትና ሲወዛገቡበት ፥ ጋዜጠኞችም የየራ

ሳቸውን መንግሥት ጥቅም በማሳነስ ፡ የሌላውን በማስበለጥ ጥቅሙንም ችግሩንም እያነሡ ሲነታረኩበት ሰንብተው ፡ በመጨረሻም የንጉሠ ነገሥቱ ድርቅ ያለው አጭር ተቃውሞ ጉዳዩን ለዘለቄታ ወድቅ አደረገው ። [1] በዚህም ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ፡ የእንግሊዝና የኢጣልያ መንግሥት የቆየውን መጥፎ አቅዋማቸውን ለመለወጥ የዓድዋ ድል ቢያስገድዳቸውም ፡ ቀድሞውኑ የታወቀ ሸካራ መሆኑን አልሳቱትም ። የፈረንሳይም ወደነዚሁ ጐራ በጥቅም መተሳሰሩ ስለገባቸው ፡ ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የፈረንሳይን ግንኙነት ቀዝቀዝ እያደረጉ እያደር ከጀርመን መንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት እያሻሻሉ በመሔድ የጀርመንን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትሩን አጉስት ፍሬደሪክ ሮዘንን አቀረቡት ። ከዚህ ጊዜ ዠምሮ የጀርመን ዐዋቂዎች በቤተ መንግሥቱ ባለሚል ሆነው ገባ ወጣ ማለት ጀመሩ ። የነርሱም አስተርጓሚ የታወቁት ከንቲባ ገብሩ ስለሆኑ በርሳቸውም አማካይነት ግንኙነቱ ሰፋ እያለ ሔደ።

የጀርመንም ዋና ምኞት ፡ ኢጣልያ እስከዚህ ዘመን ድረስ አውስትሪያ ተጨምሮ የሦስት አገሮች የቃል ኪዳን ዝምድና በሚባለው ውል ተሳስራ ከቆየች በኋላ ፡ አሁን ሸርተት እያለች ወደ እንግሊዝና ወደ ፈረንሳይ ብትጠጋም ፡ በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ከብዙ ዘመን ዠምሮ በግዛት ከተስፋፋው ከቱርክ የኦቶማን መንግሥት ጋር በመተባበር ከኢጣሊያና ከግብረ አበሮቹ መንግሥታት ጋር እየተፋለምሁ በኢትዮጵያም ፡ በሌላውም ኋላ ቀር የአፍሪካ አገር ላይ በመሠራጨት ንግዴን አስፋፋለሁ የሚል ነበር ።

የጀርመን መንግሥት ፡ በኢትዮጵያም በሌላውም የአፍሪካ ፡ የእስያና የባልካንም አገር የዚህን ዓይነት ፖለቲካ ሲከታተል ቆየ ። በመጨረሻም የአውስትሪያው መስፍን በፈረንሳይ በሚደገፈው የሰርቢያ መንግሥት ተወላጅ እጅ ተገደለ ። የዚያም ሰበብ የመዠመሪያውን የዓለም ጦርነት እ.ኤ.አ 1914—18 አስከተለ ። የጀርመን መንግሥት ከቃል ኪዳን ጓደኞቹ ከአውስትሪያና ቱርክ ጋር ሲሸነፍ ፡ እንኳን አዲስ ቅኝ አገር ሊያገኝ ይቅርና በእጁ የያዘውንም በአሸናፊዎቹ በእንግሊዝናበፈረንሳይ ተቀማ ። [2]

ዳግማዊ ምኒልክ ፡ ቀድሞ በኢጣልያ ላይ ፈረንሳይን አጋር በማድረግ እንደ ተጠቀሙ ፡ አሁን ደግሞ ፈረንሳይ ከኢጣልያና ከእንግሊዝ ጋር በኢትዮጵያ ላይ ስለ ዶለተች በፈረንሳይ ፡ በኢጣልያና በእንግሊዝ ላይ በጀርመን አጋርነት ለመጠቀም ተመኝተው ነበር ።

1 Storia Diplomatica, PP.325 - 331 .

2 L'Ethiopie et les convoitises allemandes, PP. 5—73



# ምዕራፍ ስድሳ አራት

## ዓድዋ ያስገኘው ዓለም አቀፋዊ ዕውቂያና የወሰን ስምምነት

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመታወቋ ሁኔታ ልዩ ልዩ የጊዜ ወቅት አለው ። ይኸም ባጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ይለያል ።

ሀ/ ከክርስትና በፊት ከሺ ዓመተ ዓለም ዠምሮ እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ በጥንት የግብጾችና የግሪክ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ስሟ በልዩ ልዩ መንገድ ተጠቅሶ ይገኛል ።[1]

ለ/ ከክርስቶስ ልደት በኋላ እስከ ዐሥረኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ድረስ ሥልጡኑ የአክሱም መንግሥት ፡ በምሥራቅና በምዕራብ የሮማ ቄሣሮች መንግሥት እንዲሁም በምሥራቅና በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በጣም ስሙ የገነነና የታወቀ ሲሆን ፡ ነገሥታቱ እነኢዛና በሮማ ቄሣሮች በነቆስጠንጢኖስ ዘንድ እንደ ወንድሞች ይቆጠሩ ነበር ።[2]

ሐ/ የአክሱም መንግሥት ውድቀት ካገኘው ጊዜ ዠምሮ ፡ ይኸውም ማለት ከዘጠነኛው መቶ ዓመት እስከ ዐሥራ አምስተኛው መቶ ዓመት ከልደት በኋላ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ ከውጭው ዓለም ጋር የነበራት ግንኙነት የተዳከመ ነበር ። "ቄስ ዮሐንስ በሚባል ንጉሥ የምትመራ አንድ አገር አለች" እየተባለ በአውሮፓ ቢወራም ፡ በየትኛው ክፍለ አህጉር መሆኗ አይታወቅም ነበር ። የፖርቱጋሉ ንጉሥ ዮሐንስ ዳግማዊ "ይቺን አገር ፈልጋችሁ አግኙልኝ" ብሎ እነፔድሮ ዲኮቪልሃምን ላከ ። በስንት ጥረት እ.ኤ.አ. በ1486 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ደርሶ ከዘመኑ ንጉሠ ነገሥት ከዐፄ እስክንድር ጋር መገናኘቱ በየታሪኩ ተጽፏል[3] ።

መ/ ከ16ኛው መቶ ዓመት እስከ 18ኛው መቶ ዓመት ድረስ በነበረው ጊዜ ግሪኮች ፡ አርመኖች ፡ ፖርቱጋሎችና ኤስፓኞች ወደ

1. የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጔ ፡ ተ.ጸ.መ. ፡ ምዕ 1 ፡ ገጽ 11-18 መጽ. ነገሥት 13 ፡ ዘኍልቊ 121 ፡ ምዕ. 5 ገጽ 109—140

2. Storia d' Etiopia, Conti Rossini. Chap. 5, PP. 109—140.

3. የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ፡ ተ.ጸ.መ. ፡ምዕ. 54 ።

ኢትዮጵያ መመላለስና በኢትዮጵያም መኖር ጀመሩ ። ከእነርሱም አንዳንዶቹ በተለይ፤ “ከግራኝ አህመድ ወረራ ወዲህ በተዋሕዶ ሃይማኖትና በካቶሊክ ሃይማኖት ልዩነት የተነሣ፤ ኢየሱሳውያኑ ባፄ ሱስንዮስ ዘመን በቀሰቀሱት ጦርነት ሰበብ ብዙ መጻሕፍት ስለ ኢትዮጵያ መጻፍና ያገሪቱ ሁኔታ ይበልጥ መታወቅ ጀመረ ። በዚህ ጊዜ ውስጥ በመጽሐፉ ኢትዮጵያን ለዓለም በደንብ ያሳወቀ ፍራንችስኮ አልቫሬዝ ነው ።

ሠ/ ከ18ኛው እስከ 19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ድረስ እንግሊዞች፤ ፈረንሳዮች፤ ጀርመኖች፤ መስኮቦች፤ ኢጣልያኖች በአገር ጉብኝነት መልክ ይመላለሱ ነበር ። ባፄ ቴዎድሮስ አነሣሥና ከእንግሊዞች ጋር ባደረጉት ጦርነት ሰበብ ከዚያም ወዲህ ያፄ ዮሐንስ ሁለት ጊዜ በግብፅ ጦር ሠራዊት ላይ ድል በማግኘታቸው፤ ቀጥሎም የኢጣሊያ መንግሥት ሰሜን ኢትዮጵያን በመውረሩና በውጫሌ ውል የተነሣ የበላይ ልሁን ብሎ በመከራከሩ፤ ኋላም በዐድዋ ላይ በመሸነፉ ወሬው በአውሮፓ እየተስፋፋ ስለተጻፈ፤ ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ከፊተኛው ጊዜ የበለጠ መታወቋ እየቀጠለ ሔደ ።

በኢትዮጵያ ይህ ሁሉ ሲሆን፤ ሌላው የአፍሪካ ክፍል አህጉር በአውሮፓ ኃያላን ተከፋፍሎ ተይዞአል ። ይዞታውም በ19ኛው መቶ ዓመት መገባደጃ ላይ በበርሊን የጋራ ስምምነት ተረጋግጧል ። ኢትዮጵያም ነጻ ብትሆንም ፤ አንድ ቀን ካንድ አውሮፓዊ ሥልጣን ውስጥ መውደቋ አይቀርም የሚል ግምት ነበረ ። በተለይ ቅኝ አገር ካላገኘውና ለማግኘት ከሚጣጣረው ከኢጣልያ እጅ አታመልጥም የሚል አስተያየት አልጠፋም ። በዚህም ላይ አመች ወቅት ቢፈጠር ይኸውም ማለት በኢትዮጵያ የርስ በርስ የጦርነት ትርምስ የተፈጠረ እንደሆነ አገሪቱን ከሱዳን አልፎ የአባይ ምንጭ ያለበትን ምዕራብ ኢትዮጵያን እንይዛለን የሚል ምኞት በእንግሊዞች ዘንድ ነበር ። እንደዚሁም ኢጣልያም፤ ፈረንሳይም በየበኩላቸው ለመስፋፋትና በግልጽ ሳይሆን ሰወርወር ባለ መንገድ ኢትዮጵያን ለመያዝ አጋጣሚ ጊዜ በመጠባበቅ ላይ ነበሩ ።

በዚሁ የማድባት እያያዝ የአውሮፓ ኃያላን “አንድ ቀን እንከፋፈላታለን” በሚሉ የጕጕት ተስፋ ቀደም ሲል ከኢትዮጵያ ጋር በቁም ነገር ተነጋግሮ ሌጋሲዮን ለመክፈትና የወሰን ውል ለማድረግ የፈለገ የለም ። ስለዚህ ኢትዮጵያን በየወሰናቸው ለመያዝ አመቺ ጊዜ ሲጠበቅ ፤ በመካከሉ የኢጣልያ መንግሥት ለብቻዬ እወስዳታለሁ ብሎ በቀሰቀሰው ጦርነት ዓድዋ ላይ ሊሸነፍ ቻለ ። መሸነፉን ለመበቀል የበቃ ኃይልና ጉልበት አጥቶ



በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር በ1889 ዓ. ም. በተዋዋለበት ውል ውጫሌ ላይ የተደረገው ውል በፍጹም መሠረዙንና የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን ሙሉ ነጻነት ማወቁን አረጋገጠ ። ከዚያ ወዲህ የኃያላኑ አቅዋም የተለዋወጠና ቅኝ አገር በኢትዮጵያ ዙሪያ ያላቸውም የሌላቸውም የአውሮፓ ኃያላን በአዲስ አበባ ነዋሪ መላክተኛ ለማስቀመጥ ይሽቀዳደሙ ጀመር ። ከዚህ በኋላ እያንዳንዱ መላክተኛ ሰፋፊ ቦታ እየተመራ ሕንፃ አሠራ ። ይኸም ለአዲስ አበባ ከተማ ድምቀት ሰጠ ። የመልክተኞቹም ነዋሪነት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመታወቋ ሁኔታ የተደላደለ ምስክር ሆነ ።

በዚሁ ዓይነት፤ እስከዚህ ጊዜ ድረስ በኃያላኑ ዘንድ ያልታወቀው የወሰን ክልል በዓለም አቀፍ ደረጃ ተከልሎ እንዲታወቅ ፍላጐቱ በሁሉም ወገን ተገለጠ ። መቼም ያንድ መንግሥት ጥቅሙ መኖሩ ብቻ አይደለም ። ነገር ግን፤ በመንግሥታት ዘንድ ሕጋዊ መታወቅ ሲኖረውና ግዛቱን አረጋግጦ የኔ ነው ብሎ የሚከራከርበት ዓለም አቀፋዊ የወሰን ክልል ሲኖረው ነው ። አንድ መንግሥት ደግሞ መታወቅንና ከወሰንተኞቹ መንግሥታት ጋር የመካለልን መብት የሚያገኘው፤ በከተማው የመንግሥታትን ወኪሎች ለመቀበል፤ የንግድና የወዳጅነት ውል ለመለዋወጥ ዕድል የሚኖረው፤ በቅድሚያ የመንግሥቱ አንድነትና የሕዝቡ ሕብረት ሲረጋጋ በከተማውና በየአውራጃዎቹ ሰላምና ጸጥታ ሲሰፍን ነው ።

እስከአሁን ድረስ እላይ እንዳመለከትነው፤ የአውሮፓ ኃያላን በሌጋሲዮን ደረጃ ወኪል ለማስቀመጥ ችላ ያሉት፤ ወሰን መካለሉንም ያልፈለጉት፤ አንደኛ የአንድነታችንና የጸጥታችን ሁኔታ በማያቋርጥ ውስጣዊ ጦርነት ስለሚሰናከል፤ ሁለተኛም ውስጣዊው ጦርነት ተራዝሞ ምቹ ጊዜ የፈጠረ እንደሆነ ለመውረር እንዲቻል ነበር ።

የውስጥ አንድነታችን ባፄ ቴዎድሮስና ፤ ባፄ ዮሐንስ ኃይልና ድካም ከተደላደለ በኋላ፤ ዐፄ ምኒልክ ደግሞ በፋንታቸው ኃይሉን በትዕግሥትና በሰላም ስለ አጠናከሩት የዓድዋ ለት ፤ ኢጣልያንና ምዕራባውያን ባልጠበቁት መንገድ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነመሳፍንቱ ባንድ እግር ቆሞና ባንድ የሥልጣን መስመር ተሰልፎ ወራሪ ጠላቱን መለሰ ። ከዚህም በኋላ ምዕራባውያን ኢትዮጵያ ኅብረትም፤ የጸና የመንግሥት አቅዋምም እንዳላት ተገነዘቡ ። ከዚህ ግንዛቤም በኋላ ኢጣልያና የቀሩትም የአውሮፓ ኃያላን የወረራውን ስሜት ሠርዘው ሌጋሲዮን በመክፈት ወኪል ማስቀመጥና ወሰን መካለልንም ጀመሩ ።

ኢትዮጵያን በወሰን የሚያካልሏት ፤ እንደ አሁኑ ያገር ተወላጆች የሚመሯቸው መንግሥታት እነ ጅቡቲ፤ እነ ሱማሌ፤ እነ

ኬንያ ፣ እነ ኡጋንዳ ፣ እነ ሱዳን ሳይሆኑ እነሱን ይገዙ የነበሩት አውሮፓውያን አገሮች ናቸው ። እነሱም ታላቋ ብሪታኒያ ፣ ኢጣልያና ፈረንሳይ ነበሩ ። ዐፄ ምኒልክም የወሰን ክልል የተዋዋሉት ከነዚሁ መንግሥታት ጋር ነበር ።

በዚህ መሠረት ፣ የፈረንሳይ መንግሥት በዓድዋ ጦርነት ባመቱ መጋቢት 12 ቀን 1889 ዓ.ም. አዲስ አበባ ባስቀመጠው ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር በሙሴ ሊዎንስ ላጋርድ አማካይነት ተዋዋለ ።

የኢጣልያ መንግሥትና የኢትዮጵያ መንግሥት ከዓድዋ በፊት እ.ኤ.አ. የካቲት 3 ቀን 1891 ዓ. ም. ስለወሰን ጉዳይ ተዋውለው የነበረው ኢጣልያ በውጫሌ ውል የበላይነት አገኛለሁ በማለት በቀሰቀሰችው ክርክርና ጦርነት ምክንያት ከሥራ ላይ ባለመዋሉ ፣ ከዓድዋ ድል በኋላ እ.ኤ.አ. በ1900 ዓ.ም. አዲስ አበባ የሚቀመጠው ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ካፒቴን ፌዴሪኮ ቺኮዲኮላ በኢጣልያ ንጉሥ ስም በሁለት አንቀጽ የተከፈለ የወሰን ውል ካፄምኒልክ ጋር ተዋዋለ ።

የእንግሊዝ መንግሥት በበኩሉ ፣ እ.ኤ.አ. በግንቦት 14 ቀን 1897 ዓ.ም. ጀምስ ሬኔል ሮድ በእንግሊዝ ንግሥት በቪክቶሪያ ስም ካፄ ምኒልክ ጋር የንግድና የወዳጅነት ውል ባደረገ ጊዜ ፣ በሁለተኛው አንቀጽ ላይ ሁለቱ ወገኖች በወኪሎቻቸው አማካይነት በእንግሊዝ ሱማሌ ያለውን ወደ ሐረር የሚዘልቀው መንገድ ሁልጊዜ ክፍት እንደሚሆን ፤ በአራተኛው አንቀጽ ስለቀረጥ ፣ በአምስተኛውና በስድስተኛው አንቀጽ ስለጦር መሣሪያ አገባብና አወጣጥ በጽሑፍ አስፍረውት የነበረውን መሠረት በማድረግ ፣ አሁንም ሬኔል ሮድ በእንግሊዝ መንግሥት ስም ፣ ራስ መኰንን ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ሆነው በደብዳቤ ልውውጥ የእንግሊዝ ሱማሌንና የሐረርን ግዛት በመካለል ተስማምተዋል ።

ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የእንግሊዝ መንግሥት በሱዳን በኩል ስለ አለው የግዛቱ ወሰን ሌተና ኮሎኔል ገርሀን ላን ሐሪንግተን በእንግሊዝ ንጉሥ በኤድዋርድ ሰባተኛ ስም ፣ ዐፄ ምኒልክ በራሳቸው ስም እ. ኤ. አ. ግንቦት 15 ቀን 1902 ዓ. ም. በአምስት አንቀጽ የተከፈለ ውል ተዋውለዋል ።



# ክፍል አምስት

## ከዓድዋ በኋላ የልማት ሥራ አመጣጥ

## ምዕራፍ ስድሳ አምስት

### ለልማት ሥራ ተባባሪዎች

ከዓድዋ ድል በኋላ ፣ ዐፄ ምኒልክ በድል አድራጊነት ግርማ አዲስ አበባ ገብተው ከኢጣልያ መንግሥት ጋር የመጨረሻ ውል ከተዋዋሉና የየመንግሥታቱን ወኪሎች በክብር በየተራ ተቀብለውና ሠፈር ለይተው በመስጠት ሌጋሲዮኖች ከተከፈቱ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱና የሥራ ባልደረቦቻቸው ያተኮሩት የአውሮፓን ሥልጣኔ በየመልኩ ወደ አገር ውስጥ አስገብተው የልማት ሥራ ከማስፋፋት ላይ ነው ።

በአውሮፓ እነሚካኤል ፋራዳይ የኤሌትሪክን የብርሃን ዘዴና ጉልበት ፣ እነ አሌክሳንድር ግራሃምቤል በቴሌፎን መነጋገርን አግኝተው ፣ ሌላውም ወሃን ከወንዝና ከምንጭ በቧምቧ እየጠለፉ ወደ ቤት ውስጥ በማስገባትና ወደ እርሻ ቦታ በመጠላለፍ ሰብላቸውን እያበረከቱ አገራቸውን ሲያለሙ ፤ የሕክምና ፣ የኢንዱስትሪ ፣ የሜካኒክ ሥራ በየመልኩ እየተሻሻለ ሲሔድ ኢትዮጵያ በጥንቱ ኋላ ቀር መሣሪያ ስትጠቀም ረዥም ዘመን አሳልፋለች ።

በኤሌትሪክ ብርሃን በመጠቀም ፋንታ ፣ የፀሐይ ብርሃን ከጠፋ በኋላ ለቤት ውስጥ ብርሃን ዝቅ ያለው ቤተሰብ በምድጃ የእንጨት እሳት ፣ የእራት ጊዜ በተቀጠቀጠ የድግጣና የከትከታ እንጨት ሲጠቀም ፣ ከፍ ያለው ቤተሰብ በጧፍና በሻማ ከዚያም እልፍ ሲል በኩራዝ ፣ በፋኖስ ይጠቀማል ። በጣም ከፍ ያሉ ዘመናዊ ቤተሰቦችና የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች ወደ መጨረሻው ዘመን በማሾ ብርሃን መገልገል ዠመሩ ። አውሮፓ በቴሌፎንና በፖስታ አገልግሎት ሲጠቀም ፣ በኢትዮጵያ መልእክትን በቃል ወይም በጽሑፍ ለሌላው ለማድረስ ወይም ከሌላው ከቅርብም ይሁን ከሩቅ ለመቀበል ፈጣን የሰውና የከብት ጉልበት እየተመረጠ ከወረዳ ወረዳ ፣ ከሠፈር ሠፈር

በመቀባበል ነው ። ሕክምናን በተመለከተ ከግሪኩ ከሂፖክራትስ (460
ከክርስቶስ በፊት) ዠምሮ በአውሮፓ በልዩ የቅመማ ዘዴ እየተመጣ
ጠነ በመካኒክና በቴክኒክ ምርመራ በሽተኛ ሲታከም ፣ በኛ ዘንድ
በመላና በአጋጣሚ የሥራ ሥርና የቅጠላ ቅጠል ጭማቂ መጠኑና
ፈዋሽነቱ ባልተረጋገጠ መንገድ ሲሠራበት ቆየ ። የአስማትና የድግም
ቃላት በክታብ ተደርጐ ባንገትና በደረት ሲያዝ ጤንነት እንደሚሰጥ
ይታመን ነበር ።

ሌላው አውሮፓ የሚራመድበት የሳይንስ ፣ የፍልስፍና ፣ የሥነ
ጽሑፍ የእርሻና የመሐንዲስ ደንበኛው ትምህርት ሲሰጥ ፣ በኢትዮ
ጵያ በቤተ ክህነት በኩል የሚሰጠው ብሉይና ሐዲስ ፣ ቅኔና ዜማ
ትምህርት ሆኖ ቆየ ። ይኸውም ማለት የኢትዮጵያ መሠረታዊ
ትምህርት በመንፈሳዊ ትምህርት ላይ ብቻ የተመሠረተ ሆነ ማለት
ነው ። መገበያያውም ገንዘብ ይበልጡን ሸቀጥ ለሸቀጥ ነበር ።

መቼም ይኸን የኋላ ቀርነት ሁኔታ ለማዳንና ሥልጣኔን ፣ ጥበ
ብን ባገራቸው ለማስገባት እንኳን የቅርቦቹ እነ ዐፄ ቴዎድሮስና እነ
ዐፄ ዮሐንስ ቀርተው ፣ የሩቆቹ እነ ዐፄ ልብነ—ድንግል (1500—1533
ዓ.ም.) አገራቸውን የሚያሠለጥን ጥበበኛ ከአውሮፓ ስለ መፈለጋ
ቸው ለፖርቱጋል ነገሥታት ለአማኑኤልና ለልጁ ለዮሐንስ ፣ "ሥዕል
የሚሥሉ ፣ መጻሕፍት የሚያትሙ ፣ የጥበብ ሥራ የሚያስተምሩ ሐኪ
ሞች ፣ መሐንዲሶች ወርቅና ብር ከመሬት የሚያወጡ የቤተ መንግሥት
ሥነ ሥርዓት የሚያስተምሩ ላኩልን" ሲሉ በግዕዝኛ የጻፉት ደብዳቤ
በግልጽ ይነበባል ።[1]

ዳሩ ግን ፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ሃይማኖቱና የኖረው ባህል
እየተጫጫነ ፣ የውስጥ ጦርነትም ፋታ አልሰጥ እያለ ፣ እስከ
ዐፄ ምኒልክ የንጉሠ ነገሥትነት ዘመን ድረስ ኢትዮጵያ የኋላ ቀርነ
ቷን እንደ ያዘች ስታዘግም ኖረች ። የመንግሥት መደበኛ ከተማ ከአ
ክሱም ወደ ላሊበላ ፣ ከላሊበላ ወደ ሸዋ (ደብረ ብርሃን ፣ መንዝ ፣ የረር
ቦካን) ፣ ከሸዋ ወደ ጐንደር በተዘዋወረበት ዘመን (ከ10—19ነኛ
ምዕት ዓመት) በደብዳቤና በቃል ከመመኘት በቀር ዓለም ሊሻሻል
የቻለበትን ዘመናዊዉን የሥልጣኔ ትምህርት በየዘርፉ በቁርጠኛ ውሳኔ
ባገሪቱ በየመልኩ ለማስገባት የታደለ ንጉሠ ነገሥት የለም ። ያፄ
ቴዎድሮስም ጥረት ቢጋፋት የታየው የጦር መሣሪያው ሥራ ሁኔታ
ውጤቱ አልቀጠለም ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ በአንኮበር በምርኮ ወደ ጐንደር ሔደው ቴዎድ
ሮስ ዘንድ እንደ ልጅ የእንክብካቤ እድገት እያገኙ የጦርነትና

---

1 የግራኝ አህመድ ወረራ—ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፣ ገጽ 154 — 156



የፖለቲካ ውዝግብ ባሳለፉበት ወቅት ፣ ብዙ የአስተዳደር ዘዴና ስልት
በአዕምሮአቸው አጠራቅመው ተመልሰዋል ። ጠባያቸውንም ብልህነት፣
ትዕግሥትና አርቆ አስተዋይነት ስለተዋሐደው ፣ ወደ ሸዋም ከተመ
ለሱ ወዲህ ጢትና ማታ አውሮፓ ደርሰው ከመጡት ኢትዮጵያው
ያንና በአጠገባቸው ከሚገኙት አውሮፓውያን ስለውጭ ሥልጣኔ
በመስማት ላገራቸው ለኢትዮጵያ ዕድል ፣ ለሚወዱትና ለሚወዳቸው
ሕዝብ የወደፊት ደህንነት መፍትሔው የአውሮፓን ሥልጣኔ ከማ
ስገባት በቀር ሌላ አማራጭ መንገድ እንደሌለ ተረዱት ።

ስለዚህ ፣ ከሁሉ በፊት በመሳፍንትና በመኳንንቱ ጐን የአው
ሮፓ ተወላጆች የአማካሪ ቡድን አቋቋሙ ። ከእነዚህም መካከል የስ
ዊሱ ተወላጅ አልፍሬድ ኢልግ የሚባለው የመሐንዲስነት ሙያ
ያለው ነው ። እርሱም ከሁሉ የበለጠ ተሰሚነት ያለው አማካሪያ
ቸው እንደነበረ ባለፈው ተጠቅሷል ።

ይህ ሰው ፣ ከሁሉም በይበልጥ የተመረጠበት ምክንያት ፣ በስዊስ
ተወላጅነቱ ሳይሆን አይቀርም ። ስዊስ በአውሮፓ መካከል የምት
ገኝ በፌዴራሲዮን የምትተዳደር ፣ ከፖለቲካ ውዝግብና ከጦርነት
ገለልተኛ የሆነች ፣ ቅኝ አገር በየትኛውም ክፍለ አህጉር የማት
ፈልግ ስለሆነች ፣ የዚች አገር ዜጋ የሆነ አማካሪ ምክሩ የቀና ለየአ
ገራቸው ከሚያደሉት ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ ተወላጆች የተሻለ
እንዲያውም የነዚህን ተንኮል ያለበትን የምክር ዘዴ ተፈላልጎ ምስ
ጢሩን ለምኒልክ የሚገልጽ መሆኑ አይጠረጠርም ። የኢጣልያኖቹ
የነአንቶኔሊ የነትራቬርሲ የነካፑቺ ወዳጅነት ከምን ላይ እንደ ጣላ
ቸው ንጉሠ ነገሥቱ በቅርቡ ከዓድዋ ጦርነት ዋዜማ ላይ ተረድተው
ታል ። እንግሊዛዊም አማካሪ በቤተ መንግሥታቸው በፍጹም አልታ
የም ። ይልቅስ በዚህ ፈንታ የእንግሊዞች ባላንጣ የሆኑት ፈረንሳዮቹ
እነሞንዶን ፣ አንሸፍን በተሸይ ሙሴ ሊዎንስ ላጋርድ የራሱን የመንግ
ሥቱን ሥራ እርግፍ አድርጎ ትቶ ያፄ ምኒልክ ልባዊ አማካሪያቸው
ሆነ ።

ስለዚህ ዐፄ ምኒልክ ፣ የነዚህን የውጭ አገር ተወላጅ አማካሪ
ዎች ምክር በመስማት እውጭ አገር ደርሰው መጠነኛ ዕውቀት እየ
ቀሰሙ የተመለሱትን የነግራዝማች ዮሴፍን ፣ የነነጋድራስ ዘውገን ፣
የነአቶ አጥሜን ፣ የነ አቶ መርሻ ናሁ ሠናይን ፣ የነብላታ ገብረ እግዚ
አብሔርን ፣ የነከንቲባ ገብሩን ፣ የነአለቃ ታየን ፣ የነነጋድራስ ገብረ
ሕይወት ባይከዳኝን ፣ የነአቶ ኃይለማርያም ሰራብዮንን አስተያየት
በማዳመጥ በአገራቸው የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማስገባት ታጥቀው
ተነሡ ። መስኮብ ተምረው የተመለሱት ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት

እንዲጋጣሚ ንጉሠ ነገሥቱ በሕመም በወደቁበት ሰዓት ስለሆነ ለማገልገል አልታደሉም ። ከነዚህም በቀር ከመሳፍንትና ከመኳንንት መካከል የፈረንጅን አገር በመላክተኛነት ከጐበኙት ከራስ መኰንን፣ ከደጃዝማች መሸሻ ወርቄ፣ ከሊቀመኳስ (በኋላ ራስ) ናደው በቀር የውጭውን አገር ያላዩት እነራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም፣ እነ ሊቀመኳስ አባተ ይነስ ይብዛ ሥልጣኔን በማስገባት ረገድ ተቃዋሚዎች አይደሉም ። በፈረንጅ ትምህርትና ሥልጣኔ አገባብ የተነሣ ተዋሕዶ ሃይማኖታችንና ነዋሪው ባህላችን ይለወጥብናል ብለው የሚቃወሙት የሃይማኖት ሰዎችና እነሱንም የሚደግፉት ወገኖች ቢሆኑም፣ "እምዬ ምኒልክ" እስከ መባል የደረሱት ንጉሠ ነገሥት፣ የሚያደርጉትን ሁሉ ሕዝብ እንደሚቀበላቸው ስላወቁት፣ የቴክኒኩን ጥበብ ይኸስ የሰይጣን ሥራ ነው እያሉ ከማማት አልፈው የገሃድ ተቃውሞ ማድረግ አልቻሉም ።

ምናልባት የሥልጣኔው ውጥን ከዓድዋ ድል በፊት ቢሆን ኖሮ የገሃድ ተቃዋሚ ባልጠፋ ። አሁን ግን፣ "ጣልያንን ያህል ጠላት በቅዱስ ጊዮርጊስ እርዳታ አሸንፈው ከውጭ ጠላት አዳኑን" የሚለው ዝና ከመበርከት ጋር በፍርድ ትክክለኛ ዳኝነታቸው፣ ዘወትር እየተደገሰ በሰፊው ለወታደር፣ ለካህናት ግብር በማብላት ቸርነታቸው፣ ለግላቸው ጥሬ ሀብት ወይም ርስተ ጉልት ልስብስብ አለማለታቸው በሁሉ ዘንድ ስለታወቀ መወደድን፣ መከበርን ስለሰጣቸው የሚያደርጉት ሁሉ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አገኘ ። የሹመት ደረጃ ከማዕረግ ስምና ከሽልማት ጋር የቅርብ ዝምድና፣ የነገድ ልዩነት ሳይመለከቱ መንግሥትን በቅን ልቦና፣ በንጹሕ ሕሊና ላገለገለ ሁሉ ያለ አድልዎ መስጠታቸው፣ የመኳንንቶቻቸውን ቁጥር በብዛት ሲያበረከት፣ በነዚህም ዘንድ ያደረው የንጉሠ ነገሥቱ ፍቅር ሁልጊዜ በሁሉም አካባቢ እያደገ ከመሔድ አላቋረጠም ።

ባለቤታቸውን እቴጌ ጣይቱን በመንግሥቱ የፖለቲካና የአስተዳደር ሥራ ሲያስገቡ ከመደገፍና ከማበረታታት በቀር፣ "ሴት ነሽ ምን አገባሽ" የሚለው ስሜት አልነበረባቸውም ። "ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ" የሚል ማኅተም አሠርተው በበኩላቸው የአስተዳደር የቅርብ ረዳት ሲሆኑ፣ "የኢትዮጵያ ብርሃን እኔ ነኝ እንጂ አንቺ አይደለሽም" የሚል የዝና ሽሚያ በመንፈሳቸው አላሳደሩም ።

እ. ኤ. አ. በ1900 ዓ. ም. በሙሴ አልፍሬድ ኢልግ አማካይነት ኢትዮጵያን ለመጐብኘት ተጠርቶ የመጣው ሙሴ ሔግ ለሩ የሚባለው የፈረንሳይ ተወላጅ ወደ አዲስ አበባ ከመጣ ወዲህ እስከ ወለጋ ዘልቆ የደዴሳን ወንዝና የአባይን ዳር ዳሩን ተመልክቷል ።



ከዚያም ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሰ በምኒልክ ፊት፣ "የደረሰሁባቸውን የወረዳዎች የወንዞችና የተራራዎች ካርታ በፊታቸው ዘርግቼ አብረን ስንመለካከት የጋራዲቢን ትልቁን ተራራ የምኒልክ ተራራ ብዬ ልሠይመው ነው" ብዬ ባመለከታቸው፣ "የለም አይሆንም፣ በግዛቴ በኔ የተሠየመ ሌላ ተራራ አለና ይኸኛውን ሥያሜ ለግርማዊት እቴጌ ጣይቱ አድርገው" የሚል መልስ ሰጡኝ ሲል ወዳገሩ ሲመለስ ባወጣው መጽሐፍ አስፍሮታል ።[1]

በእውነትም በዚሁ መጽሐፉ በመጨረሻው ገጽ 446 ተጥሎ በቁጥር 2 ባዘጋጀው ካርታ ላይ የጣይቱ ጋራ ዲቢ ብሎ ያመለከተው ይነበባል ። ከውጭ አገር የመጡ ዜጐችም ገጸ በረከት ለራሳቸው ሲያቀርቡላቸው ይኸኛው ለእቴጌ ይሁን ያሉበት ጊዜ እንደነበረ ባለፈው አመልክተናል ።

ይኸን የመሰለው ከቅናትና ከምቀኝነት የራቀ አሳብ ስፊነት የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ መኳንንትና መሳፍንት ባንድ የሥልጣን ዘንግ አቁሞ የአውሮፓን ኃያል መንግሥት በዓድዋ ላይ ድል ሊመታ ቻለ ። አሁንም በሚቀጥለው ምዕራፍ ተዘርዝሮ የሚገኘውን የሥልጣኔ የሥራ ዘርፍ ለመዘርጋት ሲነሡ ያለተቃውሞ በቤተ መንግሥትም፣ በቤተ ክህነትም በኩል ሊያስተባብር የቻለው ይኸው የማይናወጥ ከምቀኝነትና ከተንኮል የራቀው ዝንባሌያቸው መሆኑ አይጠረጠርም ።

1 Menelik et nous H. Le Rou, P. 420



ዐፄ ምኒልክ በመካከለኛ ዘመን ዕድሜያቸው

ለቴር ዲሞንድ



ምኒልክ በቢሾፍቱ ሐይቅ ዳር የዲናሚት ፍንዳታ ሲመለከቱ
ለቱር ዲሞንድ

# ምዕራፍ ስድሳ ስድስት

## ባለሞያ ንጉሠ ነገሥት — ልዩ ልዩ የሥልጣኔ ውጥን

መቸም ሥልጣኔ ባገር ውስጥ ለማስገባት ፣ መሪው ራሱ ለሥልጣኔ ዋጋ የሚሰጥና ራሱም በመጠኑም የዕውቀት ሙያ የፈነጠቀበት መሆን አለበት ። ባጠገባቸው የነበሩት ፈረንጆችም ምኒልክ ዋና የፖለቲካ ሰውና መልካም አስተዳዳሪ መሆናቸውን በገለጡበት ጐን ስለ ሥልጣኔ ፣ ስለ እጅ ጥበብ የነበራቸውን ልዩ ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው በመሥራት በተግባር ያሳዩ እንደነበር ይገልጻሉ ።

ሙሴ ሲልቪያን ቪኒራስ የሚባለው የፈረንሳይ ጸሐፊ እ. ኤ. አ. በ1897 ዓ. ም. ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ብዙ ጊዜ ከቆየ በኋላ ወዳገሩ ሲመለስ ባወጣው መጽሐፍ ውስጥ የሚከተለው አባባል ይገኛል።

> . . . ከዚህ ንጉሥ የማይረሳ ማስታወሻ ይዤ ተመልሻለሁ ። ግልጽና ብልህ የሆነ አስተያየት አለው ። ማናቸውንም የእጅ ጥበብና የመካኒክ ሥራ ማየት ማወቅ መረዳት ይፈልጋል ። እንደ አንድ ሰዓት ሠሪ ሰዓቶችን ሁሉ ራሱ ፈታቶ ራሱ መልሶ ይገጥማቸዋል ። የጠመንጃ ፣ የመድፍ የመትረየስ የአሠራራቸውና የአጠቃቀማቸው መንገድ በርሱ ዘንድ ምንም ምስጢርነት የላቸውም ። የግንብ ሥራን ከነ መሣሪያዎቹ እንደ አንድ የሠራተኞች ባለሙያ መሪ ያውቃል ። ባገሩ ውስጥ ከርሱ የተሻለ አርኪቴክት (መሐንዲስ) የለም ። የዕውቀት ነገር ከሆነ ጥቃቅኑን ነገር ሁሉ በዝርዝር ማወቅ ይፈልጋል ።... እርሱ ለማሠራት የደቀናቸውን ሁሉ ዝርዝር ነገሮች ለመግለጽ ለብቻው አንድ መጽሐፍ ያስፈልጋል ።[1]”

ሌላው ባጠገባቸው ብዙ ዘመን የቆየው ዶክተር ሜራብ የሚባለው ሐኪም በበኩሉ ስለምኒልክ የዕውቀትና የሥልጣኔ ፍላጐት የጻፈውን ሁሉ እዚህ ላይ ለማስፈር ጊዜና ሥፍራ አይበቃም ። እሱም እንደ ሌሎቹ ምኒልክን እንደ መስኮቡ ትልቁ ጴጥሮስ ፣ እንደ ጀርመኑ ንጉሥ እንደ ትልቁ ፍሬደሪክ ይቆጥራቸዋል ። ስለ ዕውቀታቸው ስለሥራ ወዳድነታቸው ብዙ ሐተታ ከሰጠ በኋላ ፣ “ከሚያስደስታቸው

---

1 Une Mission Francaise en Abyssinie, PP. 177-180.

ከጠበንጃ ፡ ከመድፍና ከመትረየስ ስጦታ በቀር የበለጠ የደስታ ስሜት የሚሰጣቸው ፡ ባገራቸው በኤሌትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀስ ማናቸውም የመካኒክ ሥራ መሆኑን" ካወሳ በኋላ ፡ ቪሊ ሂንዝ ጀርመናዊ ጥበበኛ የብር ገንዘብ አዲስ አበባ እየሠራ በሚያወጣበት ሰዓት ምኒልክ በቀን ሦስት ጊዜ ፡ አልፎ አልፎ አራት አምስት ጊዜ ወደ ፋብሪካው እየተመላለሱ ሥራውን ይቆጣጠሩ እንደነበር ፡ አንዳንድ ጊዜ ራሳቸው ቪስ በማዞር ፡ ሞረድ በመሞረድ ሌላውን ሁሉ እየተዘዋወሩ ብልህ የሆነ እርዳታ ይሰጡ እንደነበረ ገልጾአል ። ከሞቱም በኋላ ቪሊ ሂንዝን አግኝቶት ፡ "በምኒልክ ሞት ዓለም የተሻለውን መሐንዲስ እንዳጣ መገንዘቡን" እንደ ገለጸለት ያወሳል ።[1]

በእርግጥም ፡ ዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፡ የመዠመሪያው ያስተዳደር ዘመናቸው ያተኮረው ፡ ባገሪቱ አራት ማዕዘን እየተዘዋወሩ አገሩ በማሳመን ፡ ጸጥታ በማስጠበቅ ፡ ከማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣን ያፈነገጡትን አውራጃዎች በመሰብሰብ ፡ ከኢጣልያ ጋር ያለውን የጦርነት ውዝግብ በድል አድራጊነት አልባት ከመስጠቱ ላይ ነበር ። በዚህ ወቅት የልማት ሥራ ለማስፈጸም ጊዜውና ሁኔታው አላመቻቸውም ። አበክረው ወደ ሥልጣኔና ወደ ልማት ያተኮሩት ከዓድዋ ድል በኋላ ነው ።

ከዚያ በፊት ከአክሱም መንግሥት የገናንነት ውድቀት ወዲህ (ከ10ኛ መቶ ዓመት) በኢትዮጵያ የሚሰጠው ትምህርት ፡ በመንፈሳዊ ትምህርት ላይ የተመሠረተ ነበር ። ይኸንንም የሚከታተለው አብዛኛው ተማሪና አስተማሪ የቤተክህነት ወገን የሆነው ነው ። የትምህርቱም ደረጃ ከፊደል ዠምሮ በፊደለ ሐዋርያ ፡ በወንጌልና በዳዊት ደገማ አልፎ በቅኔ ፡ በጸዋትወ ዜማ ፡ በብሉይና በሐዲስ ፡ በሊቃውንትና በመጻሕፍት መነኮሳት ወዘተ . . . ይደመደማል ።

ይኸንንም የቤተ ክህነት ሰዎች ሲማሩና ሲያስተምሩ ፡ እንደ ውጭ አገር መምህራን በወንበር ተቀምጠው ሒሳብና ጽሕፈት ዠምግራፊ ሳይጨመር መምህሩ ከመደብ ላይ፡ ተማሪዎቹ በመሬት ላይ ሆነው ከቃል ወደ ቃል እየተላለፈ ነው ። ትምህርቱን አልፎ አልፎ የነገሥታት ልጆች በብርቅ ይከታተሉታል ። ብዙዎች በአስተዳደር መስክ የተሠማሩ አገረ ገዦዎች ፡ ዳኞች ፡ ያማርኛውን ጽሑፍ የማያነቡም የማይጽፉም ነበሩ ።

1 Impression D'Ethiopie; L'Abyssinie sous Menelik II. Dr. Merab Tome II. PP.55-57.



የሃይማኖትን ለውጥ ያስከትላል በሚሉ ሥጋት ዓለም የሠለጠነበትን ወይም ለመሠልጠን የሚሻማውን ዘመናዊውን የፍልስፍና ፡ የሳይንስ ፡ የእርሻ ፡ የመሐንዲስነት ፡ የሕክምና ትምህርት ከእጅ ጥበብ ከኢንዱስትሪው ጋር ኢትዮጵያውያን ሲሸሹት ስለኖሩ ፡ እስከ ዐፄ ምኒልክ ዘመን ድረስ ኢትዮጵያ ለአውሮፓ ሥልጣኔ በሩን ዘግታ ኖረች ። በዚህ ምክንያት በሕግ ዕውቀት የተመረቀ ኢትዮጵያዊ ከመጥፋቱ፡ የተነሣ የውጫሌ ውል በተደረገበት ሰዓት 17ኛው አንቀጽ በትርጉም የሚያስከትለውን መዘዝ አጢኖ ከመዠመሪያው ላይ ያስጠነቀቀ ያለ አይመስልም ። ከኢጣልያ መንግሥት ስለ ተበደሩት ገንዘብ ጉዳይ ወደ ሚሊዮን የሒሳብ ቁጥር ወደ ስብርባሪ ቅናሽ እየገባ ይኸንኑ ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር ራስ መኰንን ሲጻጻፉ ፡ "የዚህን ሒሳብ አቆጣጠር አለመድነውም" ሲሉ የጻፉትን ማስታወስ ይበቃል ።

ስለዚህ ዐፄ ምኒልክ ከምድር ባቡሩ ፡ ከመንገዱና ከስልኩ መገናኛ ማስገባት ወዲህ አሳባቸው በፍጹም ወደ አውሮፓ ትምህርት አዘነበለ ። ያለዚህም ምንም ዐይነት የተሻለ አኗኗርና አስተዳደር እንደማይገኝ ባለፈው ጊዜ ካፄ ቴዎድሮስ ዘመን ዠምሮ በብዙ መንገድ ተረድተውታል ። ከመዠመሪያ የነጋሢነት ዘመናቸው ላይ ቢወጥኑት በተቃዋሚ ብዛት ውጥኑ እንደሚበላሽ ስለ ተረዱት ፡ ቸል ያሉትን ከዓድዋው ጦርነት ወዲህ ከምርኮኞቹም ፡ ለርዳታ ከመጡት ከመስኰቦቹም ጋር አብሮ በመኖር በማየትና በመስማት የቤተ ክህነቱም ፡ የቤተ መንግሥቱም ባለሥልጣኖች ስለ ሥልጣኔ ያላቸው የተቃውሞ አስተያየት ላላ እያለ ሔዷል ።

ቢሆንም ፡ የካቶሊክ እምነት ካላቸው ከፈረንሳዮቹ ወይም ዐረማርያም ከሚባሉት ከእንግሊዞች መምህራንን በመፈለግ ባገር ውስጥ ጠብ እንኳን ቢቀር ቅሬታና ማጉረምረም እንዳይፈጠር ሲሉ የተዋሕዶ ሃይማኖት ከመነጨበት ፡ ጳጳስ ከሚመጣበት ከእስክንድርያ (ከግብፅ) አገር መምህራንን በገንዘብ ቀጥረው ማስመጣትን መረጡ ። ለመምህራኑም የበላይ ሹም የአቡነ ማቴዎስ የቅርብ ዘመድ የሆኑትን ፕሮፌሰር ሐና ቤይ ሳሊም የሚባሉትን በመሾም ዛሬ በስማቸው የሚጠራውን የዳግማዊ ምኒልክን ትምህርት ቤት በ1900 ዓ.ም. አቋቁመው የመሳፍንትም ፡ የመኳንንትም ፡ የደሃ ልጆችም ቁጥራቸው እስከ 150 የሚደርስ ወጣቶች ተደባልቀው ይማሩ ገጠሩ ። ለሌላው ምሳሌ ለመሆን ሲሉ ላልጋ ወራሽነት ያጩዋቸውን የልጅ ልጃቸውን ኢያሱንም አስገቡ ።[1]

1 L' Ethiopic tell e qu'ell itait en Septembre ,1935, A.Zervos,P.223.

የዚህን ጉዳይ ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ዝርዝር ሁኔታ ሳያቀርቡልን ባጭሩ እንደዚህ ብለው አልፈውታል ። “ . . . አስተማሪዎችም ከእስክንድርያ በደሞዝ አስመጥተው የተማሪ ቤት አሠርተው የመኳንንቱ ልጅ ሁሉ ያውሮፓ ቋንቋ ትምህርት ዠመረ ።”[1]

ትምህርት ቤቱ ከተቋቋመ በኋላ ፤ የቤተሰብ አባት የሆነው ሁሉ ልጁን እንዲያስተምር ፤ ሳያስተምር ቢቀር እንደሚቀጣ ንጉሠ ነገሥቱ በዐዋጅ ያስጠነቀቁት ፣ ስለ ትምህርት መስፋፋት ያላቸውን የጋለ ምኞት ይገልጻል ። በ1898 ዓ.ም. ያወጁት ዐዋጅ እንደዚህ የሚል ነው ።

ሞዓ አንበሳ . . . .

እስካሁን ማንም የእጅ ሥራ ዐዋቂ የነበረ ሰው በውርደት ስም ይጠራ ነበር ። ስለዚህ ማንም ሰው ለመማርና ለመሠልጠን የሚደክም አልነበረም ። በዚህ ጉጂ በሆነ ሁኔታ ብንኖር ቤተክርስቲያኖች ይዘጋሉ። ይልቁንም ክርስቲያንነት አይገኝም ። በሌሎች ሀገሮች እያንዳንዱን ነገር ብቻ መማር ሳይሆን አዲስ ነገሮችም ይሠራሉ ። ስለዚህ ከዛሬ ዠምሮ ለወደፊት ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ሁሉ ከስድስት ዓመታቸው በኋላ ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይሁን ። ልጆቻቸውን ለማስተማር ለማይተጉ ቤተሰቦች ወላጆቻቸው ሲሞቱ ንብረታቸው ለልጆቻቸው መሆኑ ቀርቶ ለመንግሥት ይተላለፋል ። ተማሪ ቤቶችንና አስተማሪዎችን የሚያዘጋጀው መንግሥት ነው ።[2]

ከትምህርቱ ጐን ዐፄ ምኒልክ ሌላው ያሰቡበት ጉዳይ የሕክምናው ነው ። በስማቸው የሚጠራው የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሕንፃ ከመሠራቱ በፊት ንጉሠ ነገሥቱ የራሳቸውንም ፣ የጠላታቸውንም ቁስል የሚያድኑበት በየዘመቻው አብሮ የሚዞር እንደ ዮድ ፤ እንደ ዶፈርና እንደ ታብሌት ያሉ መድኀኒቶች መኖራቸው ቢታወቅም ፤ በኢትዮጵያ ሕሙማን የሚታከሙበት ምንም ዐይነት የመንግሥት ሐኪም ቤት አልነበረም ። ነገር ግን ፣ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ለእርዳታ በመጡት የመስኮብ ሐኪሞች አማካይነት በንጉሠ ነገሥቱ አንቃቂነት ዛሬ ከቀድሞው ተሻሽሎ አገልግሎት ከመስጠት ላይ የሚገኘው የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተቋቋመ ።

በፍርድ ረገድ ፤ ቀድሞ ከያለበት የሚመጣውን አቤት ባይ ፣ ፍርድ ሰሚ አንድ አፈንጉሥ ብቻ ሆኖ ነገረተኛ ሁሉ መቸገሩን ተመልክተው ፤ ኢትዮጵያን ከስድስት አውራጃ ላይ ከፍለው ላንዱ ክፍል ሁለት ወንበሮች (ዳኞች) በመሾም የነገረተኛን ጉዳይ ለማቅለል ሞክረዋል ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 336
2 ዝክረ ነገር — ገጽ 600



ቀድሞ ወታደር በየባላገሩ እየተመራ በንብረቱ ብቻ ሳይሆን በሚስቱ ላይ ሳይቀር ይፈጽም የነበረው ግፍና በደል እንዲታገድ ሲሉ እያንዳንዱ ባላገር በምርት ከሚያገኘው እህል ከዐሥር አንዱን ብቻ እየከፈለ በጐተራ እንዲያስቀምጥና ወታደር ከጐተራው ቀለቡን እንደ ደረጃው እየተቀበለ ራሱ አብስሎ እንዲመገብ “የዐሥራት ዐዋጅ” ብለው ያወጡትና ባላገሩን ከውርደትና በወታደር ከመጠቃት ያዳኑት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ።[1]

እንደዚሁም እስከዚህ ዘመን ድረስ ሕዝቡ ሸቀጥ በሸቀጥ ግማሹም በአሞሌ ጨው በጥይት ከመገበያየቱ በቀር ለከፍተኛ ዋጋ የሚጠቀመው በመካከለኛው ምሥራቅ በ1780 ዓ.ም. አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ በገባው የአውስትሪያዋ ንግሥት የማሪያ ቴሬዛ መልክ ባለበት ብር ነበር ። በዚህም ጸጸት ተሰምቶአቸው ከፈረንሳይ ኩባንያ ጋር ተዋውለው እ. ኤ. አ. በ1894 ዓ. ም. 20,000 ብር በመልካቸው ብር ከነሸርፍራፊው አሳትመው በርሱ መገበያየት ተዠመረ ።

ባንድ ጊዜ በመዠመሪያ የታተመው አንድ ብር ፣ የብር አላድ (አጋማሽ) የብር ሩብ ፣ የብር ስምንተኛ (መሐለቅ) እንደዚህም የብር ሐያኛና ግማሽ ግራም የሚመዝንና የዚህ ዐሥራ አራተኛ ቤሳዎች ታትመው ከገበያ ላይ ዋሉ ። የብሩ ክብደት 28 ግራም ከ0.75 ግራም ሲሆን ፡ ባንድ ወገኑ “ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ 1889 (በኢትዮጵያ አኃዝ)” የሚል ጽሑፍና የራሳቸው ዘውድ የደፋ ሥዕል ሲታይ ፤ በግልባጩ ዘውድ የደፋና በቀኝ እጁ ባንዲራ ያለበት ባለመስቀል ሰንደቅ የጨበጠ አንበሳ ሆኖ በዙሪያው ፤ “ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ አንድ ብር” የሚል ጽሑፍ ይነበባል ። ከዚያም ወዲህ በፓሪስ ቁጥሩ በርከት ያለ ብር ከነቅንስናሹ ታትሞ ባገር ውስጥ ገባ ።

ይኸንን አዲስ ገንዘብ ሕጋዊ መገበያያ እንዲሆን እንደዚህ የሚል ዐዋጅ ዐወጁ ።

ሞዓ . . . ከዚህ ቀደም ነጋዴም ወታደርም ባላገርም የሆንከ ሰው ሁሉ በየገበያውና በየመንገዱ በየሥፍራው ሁሉ በጥይት ስትገበያይ ትኖር ነበር ። አሁን ግን በኔ መልክና ስም የተሠራ ብር ፣ አላድ ፤ ሩብ፣ ተሙን መሐለቅ አድርጌልሃለሁና በዚህ ተገበያይ እንጂ እንግዲህ በጥይት መገበያየት ይቅር ብያለሁ . . . ይኸንንም ዐዋጅ አፍርሶ ጥይት ርስ በርሱ ሲሻሻጥና ሲገዛዛ የተገኘ ሰው . . . ባንዳንድ ጥይት አንዳንድ ብር ይከፈል . . . ኅዳር 22 ቀን 1901 ዓ. ም. እንጦጦ ከተማ ።

2 ዝክረ ነገር ... 2ኛ እትም ፣ 1962 ዓ ም ፣ ገጽ 198

ዐዋጁ ቢታወጅም ፣ ቢበተንም ከመቶ ዓመት በፊት ዠምሮ ባገር ውስጥና በአካባቢው ሥር ስዶ የቆየውን የማሪያ ቴሬዛን ብር ፈጽሞ ሳይደመስሰው እስከ ጊዜያችን መድረሱን እናስታውሳለን ።

ከዚህም ጋር ከ1878 ዓ.ም. ዠምሮ ከእንጦጦ ወርደው ከእቴጌ ጣይቱና ከመኳንንቶቻቸው ጋር ያዳመቁት የአዲስ አበባ ከተማ ከዕለት ወደዕለት እያማረበት ሔደ ። ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌ ጣይቱ የሚቀመጡበት ቤተ መንግሥት ፣ አንድ ያማረ እልፍኝ ፣ ሠራዊቱን ግብር የሚያበሉበት ሰፊና ታላቁ አዳራሽ ፣ የእንግዳ መቀበያው ፣ የኪዳነ ምሕረትና የገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃዎች ፣ የጠላና የጠጅ ቤቱ ፣ የእንጀራና የሥጋ ቤቱ እየተለየ ተሠራ ። እንደዚሁም በቤተ መንግሥቱ ራቅ ባለው አካባቢ በጉለሌ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ፣ ከእንጦጦ በታች ራስ ዳርጌ ፣ በጊሚራ ሠፈር እነራስ ሚካኤል ፣ ከዚያም እነራስ መኰንን ዙሪያውን እነንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ እነራስ መንገሻ አቲከም ፣ እነራስ አባተ ፣ እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ . . .በየስማቸው ልዩ ልዩ ያማረ ቤት ሠሩ ። ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆነው የእንግሊዝ ፣ የመስኮብ ፣ የፈረንሳይ ፣ የኢጣልያና የጀርመን ሌጋሲዮኖች ተቋቋሙ ። በቤተ መንግሥቱ ለመዠመሪያ ጊዜ የኤሌትሪክ መብራት ሲያንጸባርቅ ፣ ወሃ ከእንጦጦ በቧምቧ መጥቶ ሲንፏፏ ፣ እቴጌ ጣይቱ ለእንግዳ ማሳረፊያ ሆቴል ሲከፍቱ ያውሬ መፈንጫ የነበረችው አዲስ አበባ በርግጥ ያንድ ሥልጣኔ የገፋ የመንግሥት መዲናነቷን እያረጋገጠች ሔደች ።

ባስተዳደር በኩል በተለያየ መልክና ሥያሜ ባለሥልጣኖች በየክፍሉ ከጥንት ዠምሮ መኖራቸው የተረጋገጠ ነው ። ዐፄ ምኒልክ የሠለጠኑት የአውሮፓ አገሮች አስተዳደር ባገራቸው እንዲገባ ስለፈለጉ ፤ ሀሥራሁለት ቢሮዎችን በዘመናዊ እቅድ በቅድሚያ አሠርተው ከጨረሱ በኋላ፣እላይ የተወጠነው የአስተዳደርና የልማት ሥራ በደንብ እንዲካሔድ ለጊዜው ከዚህ የሚከተሉትን ዘጠኝ ሚኒስትሮች ሾሙ ። 1 አፈ ንጉሥ ነሲቡ የፍርድ ፣ 2 ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ የጦር ፣ 3 ሊቀመኳስ ከተማ ያገር ግዛት ፣ 4 ነጋድራስ ኃይለ ጊዮርጊስ የንግድና የውጭ ጉዳይ ፣ 5 በጅሮንድ ሙሉጌታ የገንዘብ ፣ 6 ከንቲባ ወልደ ጻድቅ የእርሻ ፣ 7 ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የጽሕፈት ፣ 8 ቀኛዝማች መኮንን ተወንድ በላይ የሥራ ፣ 9 አፃኘ መታፈሪያ የግቢ ሚኒስትር ። [1]

1 ዝክረ ነገር ... ከ2ኛ እትም 1962 ዓ. ም. ገጽ 54



ከነዚህም በቀር ሚኒስትር ሳይሾምባቸው ባዋጅ ተቋቁመው በሥራ እስኪያጅ የሚመሩ የስልክና የፖስታ እንዲሁም የትምህርት ሚኒስቴር ተመሠረቱ ። እነዚህም በየክፍላቸው የሚተዳደሩበት ሕግና ደንብ እየተጠና በዐዋጅ መልክ ተሰጣቸው ። ከመረብ ባሻገር ካለው ክፍል በስተቀር በአገሪቱ ሰላምና ጸጥታ ሰፈነ ። አገር ለአገር የሚተላለፈው ነጋዴ ቅሚያና ዘረፋ ቀረለት ። ገበሬው ያለምንም ሥጋት ማረስ ቻለ ። የውጭ አገር ጐብኝ ሳይቀር ከአውራጃ ወደ አውራጃ የንጉሠ ነገሥቱን የይለፍ ማኅተም ይዞ ሲተላለፍ ድርጎና መሪ እየተሰጠው እንደልቡ ይዘዋወር ዠመር ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ራሳቸው በበላይ ሥራውን ሁሉ ከመቆጣጠር አልፈው አንዳንድ ጊዜ በየሥፍራው እየተገኙ በሥራው በመካፈል የእጅ ሠራተኛውን ሁሉ ስለ እንቅቁት ለግብርና ፣ ለንግድ ፣ ላስተዳደር ፣ ለመንግሥትም ፣ ለግልም የሚያገለግለው የመሣሪያ ምርት እየበረከተ ሔደ ። ቀድሞ የእጅ ሠራተኛነት ያስንቅና ያሰድብ የነበረውን ለማስቀረት ሲሉ ፣ ላሠሪዎቹ አለቆች የማዕረግ ስም ከመስጠትና ከመሸለም ጋር ሠራተኛንና ሥራውን ለማስከበር ሲሉ ቀጥሎ ያለውን ዐዋጅ ዐወጁ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ን.ነ. ዘኢት . . . . ሠራተኛን በሥራው የምትሰድብ ተወኝ ። ከዚህ ቀደም ብረት ቢሠራ ጠይብ ፣ ሸማ ቢሠራ ሸማኔ ፣ ቢጽፍ ጠንቋይ ፣ ቤተ ክርስቲያን ቢያገለግል ደብተራ እያላችሁ አርሶ ነጭን ከጥቁር (ጤፍና ሌላ ዘር) አምርቶ የሚያገባውን አራሽ ክዘውድ (ከባለ ዘውድ) ይበልጣል የሚባለውን ገበሬ እያላችሁ ነጋዴን ነግዶ ወርቁን ግምጃውን ይዞ ሲገባ አንተ ነጋዴ ገጣባ (የአህያ የበቅሎ የፈረስ) አጣቢ እያላችሁ በየሥራው ሁሉ ትሰድባላችሁ ። እጁ ምናምን ሥራ የማያውቀው ለነፋ ብልሁን እየተሳደበ አስቸገረ ። ቀድሞም ይህ ሁሉ ፍጥረት የተገኘው ካዳምና ከሔዋን ነው እንጂ ሁለተኛ ፍጥረት የለም ። ይኸ ሁሉ ካለመማር የተነሣ ነው ። አዳምንም ብላዕ በአፈ (በሐፈ) ገጽከ (በድካምህ ወዝ ብላ) ብሎታል ። ይህ ከቀረ ሁሉ ባዘንተኛ (ሥራ ፈት) ከሆነ መንግሥት የለ ፣ አገር የለ ፣ በወዲያ አገር ግን ፣ ባውሮፓ ሁሉ አዲስ ሥራ አውጥቶ መድፍ ነፍጥ (ጠበንጃ) ባቡር ቢሠራ . . . መሐንዲስ እየተባለ ፣ እየተመሰገነ ሠራተኛውም ብዙ (ቀለብ) ይጨምርለታል እንጂ በሥራው አይሰደብበትም ። እናንተ ግን ፣ እንዲህ እየተሳደባችሁ ማረሻ የሚያሾል አሳጥታችሁ አገሬን ባዶ ልታደርጓትና ልታጠፏት ነው ። እንግዲህ ግን (ለወደፊቱ) እንዲህ ብሎ የተሳደበ እኔን የሰደበ ነው እንጂ ሌላውን መስደብ አይደለም ። ዳግመኛ ግን ሲሳደብ የተገኘ ሰው መቀጫውን አንዳንድ ዓመት ይታሰራል ። ሹማምንትም አስረህ ለማስቀመጥ የሚቸግርህ እንደሆነ አስረህ (ከአውራጃ) ወደኔ ስደድልኝ ። ጥር 17 ቀን 1900 ዓ.ም. ።

ይህ ፀዋጅ፡ ንጉሠ ነገሥቱ አገራቸውን አውሮፓ ወደ ደረሰበት የልማት ደረጃ ለማድረስ ሠራተኛ፡ ሥራና የሥራ መሣሪያ መፍትሔ መሆናቸው በትክክል እንደ ገባቸው ስለሚያስረዳ፣ ብዙም ሐተታ መስጠት አያስፈልግም ። ንጉሠ ነገሥቱ አገራቸውን ለማሠልጠን፣ ላገራቸው ሕዝብ ልማትን በማልማት ሰላምና ጸጥታን ከተሻለ ሕይወት ጋር ለማውረስ ብዙ እንደጣሩ እንረዳለን ።



# ምዕራፍ ስድሳ ሰባት

## የመገናኛ መስመር ፣ የምድር ባቡር ፣ የመንገድና የስልክ መዘርጋት —የአቶሞቢል መታየት

የአውሮፓና የአሜሪካ ዓለም ፣ ከምድር ባቡርና ከአቶሞቢል በፊት በፈረስና በበቅሎ በሚሳብ ሠረገላ ሲጠቀሙ ፣ በኢትዮጵያ የቅርቡንም የሩቁንም መንገድ ፣ ተራው ሰው በእግር ፣ ከሹም ዠምሮ እስከ ንጉሠ ነገሥቱ ድረስ በፈረስና በበቅሎ ዠርባ ተቀምጠው ይጓዙ ነበር ። ፈረስ ለጉግስና ለጦርነት ጊዜ ሲመረጥ ፣ በተለይ ለዘወትር ጉዞ የሚመረጠው በቅሎ ነው ። የበቅሎውም ፀይነት እንደ ተቀማጩ ደረጃ፣ የሚጫነው የበቅሎ ዕቃ ደረጃው ልዩነት አለው ። ከሁሉ የበለጠ ሲጋር በቅሎ ይመረጣል ።

በዚህ ዐይነት ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ ከደምቢያና ከጐንደር የኢትዮጵያን የተበታተነውን አውራጃ በአንድነት ለመሰብሰብ ወደ ጐጃም ፣ ወደ ሰሜን ፣ ወደ ላስታ ፣ ወደ ወሎና ወደ ሸዋ በተደጋጋሚ የተመላለሱት ዳገት ቁልቁለቱን በእግር ፣ ሜዳውን በበቅሎ ዠርባ ነው ። ዐፄ ዮሐንስም የቴዎድሮስን መርሕ ተከትለው ይኸን አንድነት ለማጠንከር ከመቀሌ ወደ ቤገምድር ፣ ወደ ጐጃም ወደ ወሎ ፣ ወደ ደብረ ታቦርና ወደ ሸዋ በበቅሎ ተመላልሰዋል ። ከመቀሌ ወደ ሰሐጢ ጣልያንን ለመውጋት ፣ ከሰሐጢ ተመልሰው ወደ ጐጃም ፣ ከጐጃም ወደ መተማ የዘመቱትም በበቅሎ ነው ። ዐፄ ምኒልክም ከአንኮበር ወደ እንጦጦ ፣ ከእንጦጦ ወደ አሩሲ ፣ ወደ ሐረር ከዚያም ወደ ወሎና ወደ ቤጌምድር ፣ ከቤጌምድር በጐጃም በኩል ወደ ሸዋ ፣ በወሎ ፣ በአላጌና በመቀሌ በኩል ለጦርነት ወደ ዓድዋ የዘመቱትና ከድሉም በኋላ በትግራይ ወዲያና ወዲህ ተዘዋውረው በወሎ በኩል አዲስ አበባ የተመለሱት በክብት ዠርባ ላይ ነው ። በየዕለቱ በከብት ዠርባ ላይ መጓዝ የቱን ያህል አድካሚ መሆኑን ሁኔታውን የሚያውቀው ይገነዘበዋል ፣ በሰውነት ላይ ያለው የሁልጊዜ ንቅናቄና የጭንና የባቱ መደንዘዝና መዛል ፣ ካለንበት ዘመን አንጻር ሲመለከቱት አድካሚና አሰልቺ ነው።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፡ ምኒልክ ከርሳቸውና ከሕዝባቸው በአናናር የሚሻሉት አውሮፓዎች በሌላውና በዚህ በጉዞ ረገድ ያላቸውን ያና ናርና የጉዞ ዘይ ከወዳጆቻቸው ከአውሮፓ ተወላጆች ከነሙሴ ላጋር ድና በተለይ ከቅርብ የወዳጅ አገልጋያቸው ከአልፍሬድ ኢልግ ዘወ ትር ወሬውን በመስማት ማጥናታቸው አልቀረም ።

አልፍሬድ ኢልግ ፣ በስዊስ አገር ተወልዶ በማደግ በመሐንዲስ ነት ከተመረቀ ወዲህ እ. ኤ. አ. በ1878 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ከንጉሥ ምኒልክ ተገናኝቶ የቅርብ ረዳት ሆኖ ያገለ ግል ገጠመር ። በዚያን ሰዓት ወደ ንጉሡ ቀረብ ካሉት ኢጣሊያኖች ከነአንቶኔሊ ፡ ከነኪያሪኒ ፡ ከፈረንሳዮች ከነሪምቦና ከነሽፍነ ጋር ወዳጅነት ያዘ ። ፡ ላዩ ምኒልክም እያደር የቅርብ ባለሟል በመሆን እንግዳ አስገቢ ፡ ዕቃና የጦር መሣሪያ አስመጭ ሆነ ። የኢጣሊያ ኖች አጥቂነት እየበረከተ ሲሔድ ፡ ለምኒልክ ታማኝነቱን እያጸና የኢጣልያኖች ባላንጣ ከሆኑት ፈረንሳዮች ከነሽፍነ ፡ ከነሞንዶን ጋር እየተባበረ በታማኝነት ላዩ ምኒልክ አገልግሎቱን በመቀጠል በመጨረሻ የመንግሥት ዋና አማካሪ እስከ መባል ደረሰ ።

ስለዚህ ፣ ከዓድዋ ጦርነት በፊት ፀዬ ምኒልክ የአውሮፓን ሥል ጣኔ ባገራቸው ለማስገባት ከተነሣሡባቸው ዘርፎች አንዱ የዚህኑ የጉዞ ድካም የማሻሻሉ ጉዳይ ስለ ሆነ ፣ በአውሮፓ የሐዲድና የባቡር መስመር በመሐንዲሶቹ በነቪቪያን ከተገኘበት ከ1823 ዓ.ም. ዠምሮ ሲሠራበት እንደቆየ ፣ እንደዚህም ፀዬ ምኒልክ ለዓድዋ ጦርነት ሁለት ዓመት ሲቀር ለዚሁ ፣ ለወዳጅ አገልጋያቸው ለአልፍሬድ ኢልግ ከጅ ቡቲ እስከ ሐረር ፣ ከሐረር እስከ እንጦጦ ፣ ከእንጦጦ እስከ ከፋ ፣ ከዚ ያም እስከ ነጭ አባይ ድረስ የሐዲድ መንገድ እንዲዘረጋ መጋቢት 1 ቀን 1886 ዓ.ም. በተፈረመ ውል ፈቀዱለት ። በዚህ ውል ውስጥ ከ1 እስከ 3 አንቀጽ መስመሮቹ የሚዘረጉባቸውንና የውሉ ጊዜ የሚ ቆየው እስከ 99 ዓመት መሆኑን ፣ አራተኛው አንቀጽ እስከ ሁለት ዓመት ሥራው ያልተዠመረ እንደሆነ ውሉ እንደሚፈርስ ፤ አምስተ ኛው አስገዳጅ ነገር ካልመጣ በቀር የባቡሩ አካሔድ በምንም ዐይ ነት እንደማይቆም ፤ ስድስተኛው ኩባንያው የቴሌግራፍ ሥራ እንዲ ያቋቁም በዚህም የቴሌግራፍ መስመር የመንግሥት መልእክት በነጻ እንዲተላለፍ ፤ በሰባተኛውና በስምንተኛው አንቀጽ ያለ ኢትዮ ጵያ መንግሥት ፈቃድ ኩባንያው የማንኛም ወታደርና የጦር መሣ ሪያ ወዳገር ማስገባትም ፣ ካገር ማስወጣትም እንደማይችል ፣ በሰላሙ ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደሮችና የጦር መሣሪያ ሁለቱ ወገኖች በተስማ ሙበት ዋጋ እንደሚመላለሱ ፡ በጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደርና



የጦር መሣሪያ በነጻ እንደሚመላለስበት ያረጋግጣል ። በዘጠነኛ ውና በዐሥረኛው አንቀጽ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ኩባንያው ስለሚያገኙት የቀረጥ ጥቅም ፣ በዐሥራ አንደኛውና በዐሥራ ሁለተ ኛው አንቀጽ የኢትዮጵያ መንግሥት ኩባንያው ለሚዘረጋው መስ መር አስፈላጊ የሆነውን ቦታ በግራና በቀኝ ከነ ዕንጨቱ ከነድንጊ ያው እንደሚሰጥና መስመሩንም እንደሚያስጠብቅ ፣ በዐሥራ ሦስተ ኛው አንቀጽ ኩባንያው ለሐዲዱ ሥራ የሚያስመጣው ማናቸውም ዕቃ ከቀረጥ ነጻ ስለመሆኑ ፤ ዐሥራ አራተኛው የውሉ ጊዜ (99 ዓመት) ሲያልቅ ፡ ኩባንያው የባቡሩን መስመር የሚያንቀሳቅሰውን መሣሪያ ጭምር ለኢትዮጵያ መንግሥት በነጻ አስረክቦ እንደሚ ለቅ ፤ በዐሥራ አምስተኛው አንቀጽ ለዚህ ፈቃድ 10,000 ብር ንጉሠ ነገሥቱ ከኩባንያው እንደሚቀበሉ ሆኖ ፡ በጥሬው ገንዘብ ፈንታ የባለአክሲዮንነት መብት የጽሑፍ ሰነድ እንደሚቀበሉ ያረጋግጣል ።

ይኸንኑ ውል በመጋቢት 1 ቀን 1886 ዓ.ም. ከአልፍሬድ ኢልግ ጋር አድርገው እንደቆዩ ፣ ኢልግ ገንዘብ ስላጣ የፈረንሳይን መንግ ሥት በምትኩ አስገባ ። በጥር 21 ቀን 1900 ዓ.ም. የቀድሞውን ውል የሚያሻሽል በ18 አንቀጾች የተከፈለ ውል የባቡሩን ሥራ ኃላ ፊነት ከፈረንሳይ መንግሥት ከተቀበለው ከዶክተር ቢታሊያ ጋር ተዋዋሉ ። ምንም እንኳ በሰፊ ምኞት ለስሙ የሐዲዱ መስመር ከጅቡቲ እስከ ሐረር ፣ ከሐረር እስከ እንጦጦ ፡ ከእንጦጦ እስከ ከፋ ከዚያም እስከ ነጭ አባይ ድረስ መሆኑ ቢጠቀስም ፣ አልተሠራም ። ምክንያቱም በዚህ ረጅም መስመር የሐዲድ ሥራ መሥሪያና ማስፈጸሚያ በቂ ገንዘብ በመታጣቱ ይመስላል ። በቅድሚያ እስከ ድሬድዋ ድረስ በመጨረሻም ዛሬ እንደሚታየው ፣ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ብቻ ተፈጽሞ መሥራት ዠመረ ።

ፀዬ ምኒልክ ፡ የአውሮፓን የሰውና የሸቀጥ ማመላለሻ ዘዴ ባገ ራቸው ለማስገባት ይኸን የምድር ባቡር ውል ከተዋዋሉ ወዲህ የሐዲዱ መስመር ላገር ያተረፈው ጥቅም ግምቱ በብዙ አንጻር ብዙ ነው ። መስመሩ የሚያልፍባቸው ጣቢያዎች ቀድሞ ደሳሳ የሣር ክዳን ቤቶች የነበሩባቸው ወይም የከብት መዋያ ፡ ያውሬ መፈንጫ የነበሩት ከአቃቂ እስከ ደወሌ ድረስ የሚገኙት እነሞጆ ፡ እነቢሾፍቱ ፣ እነናዝሬት እነወልንጪቲ ፣ እነ ድሬዳዋ . . . የደመቁ ከተሞች ለመሆን በቁ ።

ከሐዲድ መስመር ውጭ ባገሪቱ ከተሞች የሚገናኙበት ፣ የመን
ግሥት ሠራተኛ ፣ ወታደር ፣ ነጋዴና ባላገር እንደልቡ የሚዘዋወርበት
ጥርጊያ መንገድና ድልድዮች በያለበት እንዲሠሩ ፣ በዚህ ዘመን
ጥረት መደረጉን ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እንደዚህ ሲሉ አሥ
ፍረውት ይገኛል ።

. . .የድልድይም ሥራ ከዚህ ቀደም በሀገራችን በሸዋ አይታወቅም
ነበር ። በርስትና በጉልት በከብት የተጣላ ሰው ሁሉ በጋውን እወም
በሮች (ዳኞች) ላይ ሲነጋገር ይባጃል (ይቆያል) ክረምት ሲገባ ግን ፣ ውሀ
እንዳይወስደው ከሐምሌ አቦ(ሐምሌ 5 ቀን) ወዲያ እመስከረም አቦ
(መስከረም 5 ቀን) ድረስ . . . ዳኞች እያሰናበቱት በየቤቱ ገብቶ ይከ
ርም ነበር ። በክረምትም ድንገተኛ ነገር ያገኘው ሰው ወደ ዳኛ
ሲሔድ ውሀ እየወሰደው በየመቱ ብዙ ድሀ ያልቅ ነበር ። ዐፄ ምኒልክ
ግን ፣ ይኸን ሁሉ ተመልክተው ከፈረንጅ አገር በደመወዝ ሠራተኛ
እያስመጡ በ1889 ዓ. ም. በያገሩ ፣ በየወንዙ ብዙ ድልድይ አሠሩ ።
ያባይም ወንዝ ጥንት በቀድሞ ነገሥታት (በነዓፄ ፋሲል) ተሠርቶ የነ
በረውን ድልድይ ጠላት አፍርሶት በሰባራው ድልድይ የሚሻገር ሰው
አልነበረም ። በዚህ ዘመን ግን ፣ ሠራተኛ ሰደው አባይን ሰባራውን
ድልድይ አሳምረው አስበጁት ። በዚህም ድልድይ የሚመላለሰው ሰው
ሁሉ የምኒልክን የጣይቱን ዕድሜ ያርዝም . . . እያለ እየመረቀ
ያልፋል ።[1]

ከአባይ በቀር ጸሐፌ ትእዛዝ በጽሑፋቸው ያልጠቀሷቸውን
ድልድዮች ፣ ሙሴ ሞሪስ ደኮፔና ዶክተር ሜራብ ከተጠገነው የአባይ
ድልድይ በቀር በአዲስ አበባ ከመካከል አራዳ ተነሥቶ የፈረንሳይና
የእንግሊዝ ሌጋሲዮኖች ወዳሉባቸው መንገዶች የተሠሩትን ሦስት
ድልድዮች (የራስ መኰንን ፣ የቀበናና የፍቅረ ማርያም) ድልድዮች
መሆናቸውን ደብረ ማርቆስንና አዲስ አበባን ለማገናኘት አባይ
ላይ የብረት ድልድይ ለማሠራት ታስቦ መሣሪያውም ሚላኖ
(ኢጣልያ) ካለው ኩባንያ ታዞ በማጓጓዝ እጦት ሥራው መታጐሉን
በጽሑፍ ገልጸውታል ።[2]

በዚህ ዘመን ከተደረጉት የሥልጣኔ ልማቶች መካከል ዋነኛ
ሆኖ የሚቆጠረው ፣ የስልክ መስመር የመዘርጋቱ ጉዳይ ነው ።
በመልእክት ረገድ ያለውን የከብትና የእግር ጉዞ ችግሩን ባለ
ፈው ባንጠቅሰውም ፣ ማንም አስተዋይ የሚገነዘበው ነው ። የስልኩን
አገባብ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ፣ "በ1892 ዓመተ ምሕረት ባስልክ

1. ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . .ገጽ 333—334
2. Chronique du Regne de Menelik . vol.II PP.525-526.



መነጋገር በኢትዮጵያ ተዠመረ" በማለት ወደ ዝርዝር ጉዳይ
ሳይገቡ ጠቅሰውት ያለፉትን በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ሚኒስትር የሆ
ኑት ሙሴ ሞሪስ ደኮፔ በመጠኑ ሲያብራሩ ፣ ከ1897 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.)
ዠምሮ በሁለት የፈረንሳይ መሐንዲሶች ሐረርን ከአዲስ አበባ የሚ
ያገናኝ መስመር ተዘርግቶ የነበረው ሥራውን መሥራት የዠመረው
ከሁለት ዓመት በኋላ በ1899 ዓ.ም. መሆኑን ፣ ከዚያም በተከታ
ታይ አውራጃዎችን ከዋናው ከተማ ከአዲስ አበባ የሚያገናኙ የስ
ልክ መስመሮች መዘርጋታቸውን ፣ ከነዚህም ዋነኛው መስመር አዲስ
አበባንና አሥመራን የሚያገናኘው መሆኑን ፣ በመጨረሻም አዲስ
አበባ ላይ የስልክ ማዕከልና ቢሮ በ1906 ዓ.ም. በፈረንሳዮች ሥራ
አስኪያጅነት መከፈቱን ገልጸዋል ።[1]

ጸሐፌ ትእዛዙ ፣ "ባቡርም ሠረገላም ከፈረንጅ አገር አስመጥ
ተው ካዲስ አበባ እስከ ገነት መመላለስ ተዠመረ" ያሉትንም ፣ የፈ
ረንሳዩ ሚኒስትር ደኮፔ በተለመደ የማብራሪያ ማስታወሻቸው ይህ
ባቡር የተባለው ሰርኪስ ተርዚያን የሚባሉት የአርመን ተወላጅ
በሐዲድ ላይ ሳይሆን በተሠራ መንገድ ላይ በሎኮሞቲቭ ኃይል ሊሽ
ከረከር የሚችል (እንደ አውቶሞቢል ያለ) መሆኑን ፣ ይኸንንም አስ
መጭው ሙሴ ሰርኪስ ተርዚያን ከድሬዳዋ አዲስ አበባ ለማድረስ
ብዙ ችግር እንደ ገጠማቸው ገልጸውታል ።[2]

በዚህ የባቡር አቶሞቢል ላይ ፣ ዐፄ ምኒልክ ለሙከራ በላዩ ላይ
ተቀምጠው አዲስ በተሠራው ወደ ገነት ፣ ወደ አዲስ ዓለም በሚወስ
ደው መንገድ ላይ ሲጓዙ ለሕይወታቸው የሚሳሱት መኳንንት ከኋላ
ኋላ በፈረስ እየጋለቡ ፣ "ኧረ አቁም ምን ሊያደርጋቸው ነው" እያሉ
ይጮሁ ነበር ይባላል ። ዳሩ ግን ፣ ይህም መኪና ትንሽ ጊዜ ከሠራ
በኋላ ፣ በመጨረሻ ዛሬ ሰባራ ባቡር ከሚባለው መንገድ ተገ
ትሮ እንደቀረ በዚህም ካንዲት ከዝንጉ ሴት ጠባይ ጋር በማዛመድ ፣

ቢነግሩሽ ፣ ቢነግሩሽ አታጠናቅሪ
እንደ ተርኪስ ባቡር ተገትረሽ ቅሪ ።

ተብሎ ተገጥሟል ።

ዐፄ ምኒልክ ፣ በዚህ ዐይነት የመንገድና የስልክ ፣ የመገናኛ መስ
መር በያለበት ሲዘረጉ ፣ ድልድዮች ሲያሠሩ ፣ የቤተ መንግሥታቸ
ውን እልፍኝና አዳራሽ ባዳዲስ ሕንፃ ሲያሳንፁ ፣ ሥልጣኔ ወዳድ

1. Chronique du Regne de Menelik . . . . PP.484- 485, No. 2.
2. Idem

የሆነው ሁሉ በሥራቸው ተባባሪ ከመሆን ጋር ሥራቸውን ከማድነቅና ከማስደነቅ አልቦዘነም ። ግማሹም የደስታ ስሜቱን በግጥም እንደዚህ እያለ ገልጾላቸዋል ፤

ባቡርም ተሜነ ስልክም ተናገረ
ይኸ በማን ጊዜ ተደርጎ ነበረ
ምኒልክ ነቢይ ነው ሆዴ ጠረጠረ
የሐበሻው ንጉሥ ምኒልክ ነቢይ ነህ
ኃላፊውን ትተህ መጭውን ታውቃለህ ።

እንዳንድ የቤተ ክህነትና የቤተ መንግሥት የዋሃን የሆኑት ባለሥልጣኖች የስልኩንም ፥ የመኪናውንም ሥራ የሰይጣን ሥራ ነው እያሉ ያጉረመረሙት እያደር የምኒልክን አያያዝ የተሠራውን ሁሉ የሚሰጠውን ጥቅም በመገምገም ፥ ሌላው ሲያደንቅ የነርሱ ኩርፊያ ዋጋ እንደሌለው በመረዳት ፥ በግድም በውድም በመጨረሻ የሥልጣኔው እርምጃ አባሪ ተባባሪ ወደ መሆን አዘነበሉ ።





የዐፄ ምኒልክ አማካሪ እንጂኒዬር አልፍሬድ ኢልግ

ከክሪስፒ መጽሐፍ